

ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

# ትንሣኤ



ተራዳኢው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት እንዳዳናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ገጽ

አርእስት

ደብዳቤዎች ............ ፭
ለዓለም ሁሉ የሚሆን ደስታና ሰላም ............ ፮
ቅዱስ ገብርኤል ............ ፯
ትንቢት ቅድመ ልደት ............ ፰
ጤነኛና ጥሩ ዜጋን ለማፍራት ............ ፰
ደግ ልጅ ስጠኝ ............ ፱
ትምህርተ ግዕዝ ............ ፲
ዜና ሊቃውንት ............ ፲፫
ምን እንርዳዎ ............ ፲፬
የቄስ ሚስት አልሆንም ............ ፲፯
የግዕዝ ትምህርት በመንፈሳውያን ት ቤቶች............ ፲፱
የጾመ ነቢያት ስሙና ብያኔው ............ ፳
በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ ............ ፳፮
ይህን ያውቁ ኖረዋል? ............ ፳፰
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን ለምን እስከ ዛሬ ድረስ አላሳተመችም ?

2ኛ በገጠር ባለችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናት በሙት ልብስ ይቀድሳሉ ። በከተማ ግን እያንዳንድዋ ቤተ ክርስቲያን በብዙ መቶ የሚቆጠር ልብሰ ተክህኖ አላት ስለዚህ የከተማዋ ለገጠርዋ ቤተ ክርስቲያን ለምን በብዛት ካላት ልብሰ ተክህኖ አታካፍልም?

ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ
ከአቃቂ በሰቃ ሸዋ

ዲያቆን ጥላሁን ያቀረቡት ጥያቄ መልካም ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ ብሉይና ሐዲስ ኪዳናት በአንድነት አሉአት። እነርሱም በ1931 ዓ.ም. በአንድነት ታትመዋል አሁንም በመባዛት ላይ ስለሆኑ ወደፊት በማንኛውም ክርስቲያን እጅ እንደሚገቡ ተስፋ አለ ። እስከዚያም ድረስ በግእዝም ሆነ በአማርኛ ለየብቻ ታትመው በሚገኙት ብሉይና ሐዲስ ኪዳናት መጠቀም ይቻላል ። ከዚህም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ የሰዎች ወይም የድርጅቶች አይደለም ። ስለዚህ ይህ የኦርቶዶክስ ነው ያ የእነዚያ ነው በማለት የእግዚአብሔር የሆነውን ገንዘብ ለሰዎች ማካፈል ተገቢ አይመስልም ። እርግጥ ሰዎች እንደ ገዛ ፈቃዳቸው በማጣመም የተረጐሙትን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመቁጠር ለመቀበል አልተፈቀደም ።

በሁለተኛው ጥያቄ የተመለከተው የገጠር አብያተ ክርስቲያናት የልብሰ ተክህኖ ጉዳይ ነው እርስዎ የመቀደሻውን ልብስ ተመለከቱ እንጂ በቤተ ክርስቲያኑም አሠራር በኩል ትልቅ ልዩነት አለ ለምሳሌ የገጠሩ ቤ ክርስቲያን በሰንጨት ጨፈቃ የተሠራ በጭቃ የተለሰነ በገለባም የተከደነ ነው ። የከተማው ግን በድንጋይና በዕብነ በረድ የታነፀ ነው ።

ታዲያ በዚህ አንጻር በልብሰ ተክህኖ ልዩነት ቢኖር አያስደንቅም ቤተ ክርስቲያን የምትቋቋመው በምእመናኑ የኑሮ ደረጃ ነውና ። ነገር ግን የከተማና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አድባራትና ገዳማትም አንድ አይነት ማዕከላዊ የአስተዳደር ሥርዐት ቢኖራቸውና ሁሉም የሚያገኙት ገንዘብ በአንድነት ሆኖ እንደገና ለሁሉም በእኩልነት የሚካፈል ቢሆን ልብሰ ተክህኖ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ንዋየ ቅድሳት ሊሟላ ይችላል ። ነገር ግን እንደዚህ እስከሚሆን ድረስ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን መስቀልና ሥዕል ይዘው የከተማ አብያተ ክርስቲያናትን መለመናቸው ስለማይቀር በልመናም ችግራቸውን ማስወገድ ስለማይችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቢያስቡበት መልካም ነው ።

☆☆☆

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አንድ ሰው ሲታመም እሞታለሁ በማለት ቀሳውስትን ጠርቶ አቁርቡኝ ይላል ። ቀሳውስቱም ሥርዐተ ቁርባን ና ትምህርተ ሃይማኖት ሳያስተምሩ በህመሙ ምክንያት ያቆርቡታል ። ገንዘብም ይከፍላል ይባላል ። ገንዘብ መክፈሉም ሆነ በጤናማነቱ ጊዜ ያልፈለገውን ቅዱስ ቁርባን በታመመ ጊዜ መቀበሉ ተገቢ ነው ?

ተድባበ ማርያም እሸቴ
አ.አ.

ተድባበ ማርያም የወንድ ወይም የሴት ስም እንደሆነ ጠያቂው ግልጥ አላደረጉትም ። ሆኖም በጌታችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታችን ይድረስዎ ጥያቄዎም እንደሚከተለው ተመልሶአል አንድ ሰው በታመመ ጊዜ ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበል ቢጠይቅ ሊያቀብሉት እንደሚገባ በቤተ ክርስቲያናችን የሥርዐት መጽሐፍ ተፈቅዶአል በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 13 ፡ 506 ላይ እንደሚከተለው ተጽፎአል "ከምእመናን ወገን በውጭ ያለ ሰው ቢኖር ታሞ ዕለተ ሞቱ ቢቀርብ ቁርባን አይከልክሉት" ።

በመሠረቱ አንድ ሰው በታመመ ጊዜ ወደ ዶክተር መሄድ ግድ ያስፈልገዋል እንደዚሁም ከሥጋዊና መንፈሳዊ በሽታው እንደሚፈውሰው አምኖ ሥጋውና ደሙን ለመቀበል የፈለገውን ሰው ሊያቀብሉት ይገባል። ይህም በመጀመሪያ ክርስቲያን ሲሆን ነው እንጂ ለማንኛውም አይደለም ። አንዳንድ ሰዎች በጤንነታቸው ቅዱስ ቁርባንን የማይቀበሉ ንቀው ወይም ተጠራጥረው ሳይሆን ራሳቸውን ለመመርመር ነው ታዲያ በዚህ እንዳሉ ቢታመሙ ሊከለከሉ እንደማይገባ እላይ የተጠቀሰው ሕግ ያመለክታል ።

ገንዘብ የመክፈሉ ነገር እውነት አይመስልም ። በቤተ ክርስቲያናችንም የሥርዐት መጽሐፍ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበለው ሰው ገንዘብ ይክፈል የሚል ትእዛዝ የለም ። አቁራቢዎች ካህናትም ክፈሉ አይሉም ። ግን ቆራቢዎች ሁሉ በፈቃዳቸው ለካህናት ግብዣ ያደርጋሉ አንዳንዶቹም እህልና ውሃ ማዘጋጀት ሳይችሉ ለምሳ ይሆናቸው ዘንድ ገንዘብ ይሰጣሉ ። ይህም በካህናቱ ጥያቄና በቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ሳይሆን በምእመናኑ ፈቃድ ነው ።

ነገር ግን ገንዘብ ክፈሉ ካልከፈላችሁ አናቆርብም የሚሉ ቢኖሩ ከቤተ ክርስቲያንዋ መመሪያ ውጭ የሚሠሩ ናቸው ።

☆☆☆

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አንድ ሰው ያገባትን ሴት ቢፈታ ወይም ብትሞት ሌላዋን ልጃገረድ በተክ

ወደ ገጽ ፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

## ለዓለም ሁሉ የሚሆን ሰላምና ደስታ

"ሕፃን ተወልዶልናል ፡ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል ፡ እርሱም አለቅነት በጫንቃው ላይ ይሆናል ፡ ስሙ
ም ድንቅ መካር ኃያልአምላክ ፡ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ። ከዛሬ ጀምሮ እስከዘላለም
ድረስ በፍትሕ አፅንቶ ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል ፡ ለሰላሙም ፍጻሜ
የለውም" ኢሳ. 9፥6-7 ፦

ይህ ቃለ ትንቢት ስለማን እንደተነገረ ዓለም ሁሉ ያውቃል የሰላም መሠረት ክርስቶስ መሆኑን በግል
ጥ ያመለክተናልና ነው ።

በመሠረቱም በመጀመያው ሰው በደል ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ አንስቶ የሰው ዘር
ሁሉ የመንፈስ ዕረፍትና ሰላም አግኝቶ መኖር የቻለበት ዘመን አልነበረም ። የሰው ዘር ሁሉ የተፈጥሮ ግንዱ
ከረገ ትውልዱ አንድ ሆኖ ሳለ እርስ በርሱ በጐሣ በቋንቋ በባህልና በመልክዐ ምድር በቀለምና በመ ሳሰለው
ሁሉ እየተከፋፈለ በሄደ መጠን ከዕለት ግጭት እስከ ዓለም አቀፍ ጦርነት በታሪክ የተመዘገበውን ብጥብጥ ሁሉ
ይህን ሰላም
በመፍጠሩ ዓለም እንደጐሸና እንደደፈረሰ በደም ተበክሎ መኖሩ አያከራክርም ታዲያ ይህን ሰላም
ዓለም ማረጋጋት ከሰው ዘር ሁሉ አቅም በላይ በመሆኑ ሌላ አንድ ኀይል አስፈለገ ። ይኸውም ቅድመ ዓለም
የነበረና ይህን ዓለም የፈጠረ የዓለም መድኅን የሆነው እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ቅ ድንግል ማርያም
ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በተዋሐደው ሥጋ በራሱ ፈቃድ በአካል የመገለጡና የመታየቱ ምስጢር በተ
ስፋ የሚጠበቅ ነበር ። ይህኑ ቀደም ብለው በትንቢት አትልተው ከተናገሩት ነቢያት መካከል አንዱ ኢሳይያስ
ስለእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን በተነበየው በዚህ ግልጥ ቃለ ትንቢት ውስጥ እንደተናገረ በተለይ "የሰላ
ም አለቃ ተብሎ ይጠራል ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም" የተሠኙት የተስፋ ቃላት ብቻ ሳይሆኑ በተግባር የተተረ
ጐሙ ሆነው እናገኛቸዋለን ። ይህም ሰላም

አዎ በክርስቶስ አዳኝነት ያመነ ሁሉ ዘላለማዊ ሰላምና የመንፈስ ዕረፍት ደስታም አለው ። ይህም ሰላም
በኃይል አስገዳጅነት ወይም የሰው ዘር ለራሱ ማጥፊያ በሚያዘጋጀው የጦር መሣሪያ ኃይል ሳይሆን በክርስቶስ
ያመኑ ሁሉ የፍጹም ወንድማማችነት ኅብረት በመፍጠር በፍቅር የሚኖሩበት መንፈሳዊ ሕይወት ነው ። ስለዚ
ህም ነበር እርሱ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአስተማረው ቃለ ወንጌል « ሰላምን እተውላ
ችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ይኸውም እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ዓይነት አይደለም" በማ
ለት እርሱ ለሚያምንበት የሰው ዘር ሁሉ የሚሰጠው ሰላም ሰዎች በራሳቸው ኃይል ብቻ ተፍጨርጭረው ለማ
ስገኘት ከሚሞክሩት ጊዜያዊ ሰላም የተለየ መሆኑን በግልጥ ያመለከተው ። ዋናው

በመሠረቱ የሰው ዘር ሁሉ ሰላምና የመንፈስ ዕረፍት አጥቶ እርስ በርሱ ሲታወክ የሚኖርበት
ምክንያት የፍቅር መጓደል ነው ። ፍቅር ሲጎድል አንዱ የሌላውን ጥቅም መፈለግ በርሱ ላይ ሊደርስበት የማይ
ፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ እንዲደርስ ማድረግ አንዱ የሌላውን መብት መንካት በፍትሕ ማዳላት ፡ ዘረኝነት
የመሳሰለው ርካሽና መናኛ አመለካከት ያድርበታል ። ከዚህም የተነሣ አንዱ ሌላውን በጠላትነት በመመልከት
ራሱ ሰላም አጥቶ የሌሎችን ሰላም ማደፍረስ በሚፈልግበት ጊዜ ተጋፊ ኃይልን በሕጋዊ ኃይል መከላከል
ግድ ሆነ ። ዳሩ ግን በዚህ ዓይነት ሒደት ዓለም በጦርነት እሳት ከመለብለብ አልፎ የአንዲት ቀን እፎይታ ያገኘ
በት ጊዜ የለም ። ይህም ሁሉ በሃይማኖታዊ አመለካከት የኀጢአት ውጤት ነው ከማለት በቀር ሌላ ትርጉም አል
ተሰጠውም ።

ከዚህ ሁሉ ይልቅ ዓለም የሰላም አለቃ የሆነውን የክርስቶስን ዓላማ በመመልከት ዐሠረ ፍኖቱን በመከተል
ክርስቶስ የሰጣትን አዲስ የፍቅር መሠረት ብታጸና የሰው ዘር ሁሉ በተፈጥሮው ወንድማማችና እህትማማች የ
መሆኑ ትርጉም በተግባር ግልጥ ሆኖ ለመታየት በበቃ ነበር ። በብዙ መንገድ የተወጠነው በሰላም አብሮ የመኖ
ር ዘዴም ሁሉ ብዙ ጊዜ ውሉ እየጠፋ የባሕር አዙሪት ዓይነት ሆኖ ባልቀረም ነበር ።

ይሁን እንጂ የጸጋ ዘመን አሁን አላለፈም የዘላለም አምላክ የሆነ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬ ወደፊትም
ለሰው ዘር ሁሉ ያለው ፍቅር የማይለወጥ ሕያው ነው ። እርሱ ምን ጊዜም ለሚወዱት ሰላምንና የመንፈስ ዕረፍት
ን መጽናናትንም ይሰጣል ። ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም የተባለው ስለዚሁ ነው ።

ምድራዊ ተድላ ደስታና የቅንጦት አኗኗር ወይም የሀብት ብዛትና ሹመት ሽልማት፡የዕውቀትም ክምች
ትና ጥበበኛነትም ብቻውን የመንፈስ ዕረፍትና ሰላምን አያስገኝም ። ዘላለማዊ ሰላምና የመንፈስ ደስታን መ
ጽናናትና መረጋጋትን የሚሰጥ ክርስቶስ ነው ። ስለዚህም ነበር የጌታ መልአክ ወደቤተ ልሔም እረኞች ቀርቦ
"እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም
ጌታ የሆነ ክርስቶስ ተወልዶላችኋል" ሲል የመሰከረላቸው ። ታዲያ ብዙ የሰማይ ሠራዊትም ከመልአኩ ጋር አ
ብረው ነበሩ ። እነርሱም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ " በላይ በአርያም ለሚኖር ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን
ሰላምም በምድር ይንገሥ ለሰውም በጎ ፈቃድ" እያሉ ሲዘምሩ ታይተዋል ። እንግዲህ በየዓመቱ ታኅሣሥ 29
ቀን የምናከብረው የጌታችን መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት በሰዎችና በሰዎች በእግዚአብሔር
ና በሰዎችም መካከል ጠፍቶ የነበረው ሰላም መገኘቱን ያሳስበናል ።

ይህም ዕለት የዓለም መድህን ክርስቶስ የሰውን ዘር ከኃጢአት ባርነት ነፃ ለማውጣት እንደሚመጣ ከብ
ዙ ሺህ ዘመናት በፊት የተነገረው ትንቢት እሙን የሆነበትና የተቆጠረው ሱባኤ ሞልቶ አምላካዊ ተስፋ የተፈጸ
መበት ስለሆነ የተለየ ክብር አለው ። "በተወደደ ሰዓት ጩኸትህን ሰማሁ ፡ በመዳንም ቀን ረዳሁህ" ተብሎ
በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት እሙን የሆነበት ይህ ዕለት ነው ።

እንግዲያውስ "እነሆ ያ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው የመዳንም ተስፋ የተፈጸመው በዛሬዪቱ ዕለት
ነው ። ምስጋናው በሰማይና በምድር የመላ ዘላለማዊ ሕያው የሆነ አምላክ በሥጋ የተገለጠበት በእግዚአብሔ
ርና በሰው ዘር መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ ፈርሶ ዕርቅ የተመሠረተበት የሰላም መሠረት የተጣለው በዚ
ህች ዕለት ነው ። ይህም ሰላም በመልክአ ምድር ወሰን የሚከለል ሳይሆን በምድር ሁሉ ለመላው ዓለም የተሰጠ
በመሆኑ በአርያም ለሚኖር ሕያው አምላክ ክብርና ምስጋና ይሁን ።

## የጾመ ነቢያት

ከገጽ ፲፬ የዞረ

መጾማቸው ቀርቶ ኅዳር 19 ቀን እንዲጀ
መር ሃሳብ ቀርቦ እንደነበር ይነገራል ።
ይኸውም "ወበዛቲ ዕለት ጥንተ ጾመ
ስብከት ገና ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ሎቱ ስብሀት በሀበ ኩሎሙ
ክርስቲያን ሮም ወአፍርንጊ ወሶርያ ወአ
ርማንያ ዘእንበለ ግብፅ ወኢትዮጵያ ጠ
ኖባ » በአለው ይታወቃል ስንክሳር ኅዳ
ር 19 ቀንተመልከትስለዚህ ከላይ የተጠቀ
ሱት ማለት ያብሳሪ የተበሳሪና የመበስ
ር በዓል ተብለው እንዲከበሩ የተደረጉ
ት ቀኖች በመጨረሻ ጾመ አብርሃም ሰሪ
ያዊ ተብለው ከጾመ ነቢያት ጋር አብረ
ው እንዲጾሙ ተደርጓል ይኀውም አቡ
ሻክር ጾመ ሀርቃልን ከጾመ አርባ ጋር
እንዲጾም ሊቃውንት የተስማሙበት
ለመሆኑ « ወአስተላጸቅዎ ለጾመ ሕር
ቃል ምስለ ጾመ አርባ ቅድስት » ሲል
እንደገለጸው ሁሉ ይህንንም «ወአስተ
ላጸቅዎ ሊቃውንት ለጾመ አብርሃም ሶ
ሪያዊ ምስለ ጾመ ነቢያት » ሲል ጠቅሶ
ወስዶታል ከአቡ ሻክር መምሬ ያገኘ
ሁት የእጅ ጽሑፍ የታሪክ መጽሐፍ ገ
ጽ 10 ።

መልአከ ኃይል ወ/ ያሬድ መኩሪያ





www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ገብርኤል

ቅዱስ ገብርኤል ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ሲሆን በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቆም የጌታ ባለሟል የሆነ ታማኝ መልአክ ነው ከጥንትም ጀምሮ በአገልግሎት ሰጪነቱ ፣ በፈጥኖ ደራሽነቱና በተራዳኢነቱ በአማላጅነቱም በምእመናን ዘንድ የታወቀ ነው ።

በብሉይና በሐዲስ ዘመን በስሙ ለተማጸኑና በአማላጅነቱ ላመኑ ሰዎች ሁሉ የፈጸማቸውን ድንቅ ሥራዎች በአጭሩ እንገልጻለን ። የቅዱስ ገብርኤልና የቅዱስ ሚካኤልን ድርሳኖች በምናነብበት ጊዜ በተግባር ኢፈጸጸም በኩል ተወራራሽ ሆነው እናገኛቸዋለን ።

ይሁን እንጂ መካኖች ልጅ እንዲወልዱ በማብሰርና አንዳንድ ቅዱሳንም ራዕይ እንዲያዩ የሚረዳ አብዛኛውን ጊዜ ገብርኤል ሆኖ እናገኘዋለን ።ይህንን ለማወቅ ቢፈለግ "ማኑሔ የሚባል አንድ ሰው ነበር ። ሚስቱ መካን ነበረች ልጅም አልወለደችም የእግዚአብሔር መልአክ ለሴቲቱ ተገልጦ ትፀንሻለሽ ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ አላት ይህንንም ለባልዋ ነገረችው እርሱም ስለተጠራጠረ እንደገና የእግዚአብሔር መልአክ ለሴቲቱ በእርሻ ስትሰራሳለች ተገለጠላት ማኑሄም ከእርስዋ ጋር አልነበረም ሄዳም ከአሁን ቀደም ያየሁት ሰው እንደገና ተገለጠልኝ ስትል ነገረችው ።

ማኑሄም ሄዶ ከዚህች ሴት ጋር የተነጋገርክ አንተ ነህን? አለው ፣ አዎ እኔ ነኝ አለው ማኑሄም ቃልህ በደረሰ ጊዜ ለልጁ የምናደርግለት ምንድነው? አለው ። የእግዚአብሔርም መልአክ ማኑሄን ሴቲቱ ከነገርኋት ሁሉ ትጠንቀቅ የወይን ጠጅ የሚያሰክርንም ነገር አትጠጣ ርኩስም ነገር ሁሉ አትብላ ያዘዝኋትን ሁሉ ትጠብቅ አለው ማኑሄም የእግዚአብሔርን መልአክ ነገርህ በደረሰን ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን ነው? አለው የእግዚአብሄርም መልአክ ስሜ ድንቅ ነውና ለምን ትጠይቀኛለህ አለው መጽሐፈ መሣፍንት ምዕራፍ 13 ከቁጥር 1-18 ።

ይህም የእግዚአብሔር መልአክ የተባለው ቅዱስ ገብርኤል ነው በዚህም መልአክ ብስራት ከሁለቱ መካኖች የተወለደ ልጅ በሐይሉና በጀግንነቱ የታወቀ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠላት ነፃ ያወጣው ሶምሶን ነው ማኑሄም ስምህ ማነው ብሎ በጠየቀው ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ስሜ ድንቅ ነው እንዳለው ተረድተናል በእርግጥም ቅዱስ ገብርኤል ለሰው ልጅ በሚሰጠው አገልግሎትና በሚፈጽመው ተግባር ሁሉ ስሙ ብቻ ሳይሆን ስራው ሁሉ ድንቅ ነው ተአምራቱም አስደናቂ ነው ።

በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ቅዱስ ገብርኤል ሁለቱን መካኖች በቤታቸው ብቻ ሳይሆን በሚሰሩበት እርሻ መካከል እየተገኘ መርዳቱ ነው ይህም የሚያሳየው በቤትና በፀደ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሰራተኛ በእርሻው በፋብሪካው ፣ በቢሮው በጠቅላላው በሚሰራበት ስራ ሆኖ በስምነው ተግባሩን የሚፈጽምለትና ብጽአቱን የሚያደርስለት አማላጅነቱንም የሚያከናውንለት መሆኑን ከላይ የተፈጸመው ድርጊት በቂ መረጃ ሊሆን ይችላል በተጨማሪ ሴትየዋ በእርግዝናዋ ወራት የሚያሰክር መጠጥ እንዳትጠጣና ከርኩስ ነገር ሁሉ እንድትከለከል ምክር መስጠቱ ሌላው አስደናቂ ነገር ነው ይህም ሴቶች የሆኑ ሁሉ በእርግዝናቸው ወራት የሚያሰክር መጠጥ እንዳይጠጡ ታላቅ ምክር የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪም ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ ርኩስ የሆነውን ነገር ሰራሱ እንዳይጠቀምበትና ብጽአትም አድርጐ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይወስድ መሆኑን ያሳያል ።

ቅዱስ ገብርኤል ለመካኖች ብቻ ማብሰር ሣይሆን የሚፀልዩ ቅዱሣንንም ከእግዚአብሔር እየተላከ በራዕይ ያነጋግራል ካነጋገራቸውም መካከል አንዱ ዳንኤል ነው እሱም እንዲህ አለ"እኔም ገና ስናገርና ስጸልይ በኃጢአቴና በሕዝቤም በእስራኤል ኃጢአት ስናዘዝ በአምላኬም በእግዚአብሔር ፊት ስለተቀደሰው ስለአምላኬ ተራራ ስለምን ገና በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራዕይ አይቸው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ በማታም መስዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ አስተማረኝም ተናገረኝም" ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 9 ከቁጥር 20-23 ።

ቅዱስ ገብርኤል በጸሎትና በሀልም የነበረውን ዳንኤልን እንዳነጋገረውና እንደዳሰሰው ሁሉ ዛሬም ቢሆን በችግር ፀዘቅት ውስጥ ወድቀው የሚጸልዩትንና የሚለምኑትን አማኞች ሁሉ ይረዳቸዋል ። ከችግር አዘቅትም ያወጣቸዋል ያነጋግራቸዋል ለምህረት ፣ ለቸርነት ፣ ለበጎ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ አማኞችን እንዲረዳ በየቀኑ የሚላክ የሰላም መልእክተኛ ነውና ።

በዘመነ ሐዲስ ደግሞ ስለ መጥምቁ ዮሐንስና ስለ ክርስቶስ ልደት የተላከና ያበሠረ ይኸው ቅ ገብርኤል ነው።ብዙ ተግባሮችን እንደፈጸመ ከቅዱሳት መጻሕፍት እናገኛለን ። ከብዙዎቹ አንዳንዶቹን ብንገልጽ " በቂሳርያ ቆርኔሌዎስ የሚባል ሰው ነበር እርሱም ከቤተሰቡ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ፣ ለሕዝቡም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ፣ ወደ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚጸልይ ነበር ። የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ር እርሱ ሲገባ በራዕይ በግልጽ አየው እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ ጌታ ሆይ ምንድነው? አለ ። መልአኩም ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ አለው" የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ከቁጥ 2-4 ።

ይህንንም መልአክ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ቅዱስ ገብርኤል እንደሆነ ይነገራሉ ዛሬም ቢሆን እንደ ቆርኔሌዎስ ያሉ እግዚአብሔርን ለሚ

በገጽ ፮ ይመልከቱ



# ትንቢት ቅድመ ልደት

"ትንቢት ነገርን ይቀድመዋል" እንደሚባለው ለሚሠራው ሥራ ሁሉ በመጀመሪያ መታሰብ መነገር አለበት፣ አስቀድሞ ሳይታሰብና ፡ ሳይነገር የሚሠራ ሥራ ግን ድንገተኛ ነውና ውጤቱ ሊያምር አይችልም ።

ኀሕ ሳይቀድ ፀሐይ አይወጣም ፡ ደመና በአየር ላይ ሳያንዣብብ ዝናም ሊዘንም አይችልም ፣ ዘርም በመሬት ላይ ካልወደቀ ቡቃያ አይታይም በዚህ መነሻነት ለመግለጽ የፈለግሁት ለጌታችን ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ተቀዳሚዎች ሆነው ስለተነገሩት ትንቢቶች ነው ።

ለክርስቶስ ሁለት ልደታት አሉት አንደኛው ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ የተወለደው ልደት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ያለ አባት የተወለደው ሥጋዊ ልደት ነው ፣ ተወለደ ለማለት ተጸንሰ ፣ ተጸነሰ ለማለት በቅድምና ነበር ማለት ይቀድመዋል እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንገት አልተወለደም ከመምጣቱ አስቀድሞ ብዙ ትንቢታት ተነገረዋል ፡ ብዙ ምሳሌዎችም ተመስለዋል ።

ለምሳሌ አንድ ሀገርን ለመጐብኘት የሚሻ ባለ ሥልጣን ከራሱ ሀገር ከመነሳቱ አስቀድሞ ታሪኩ እንዲነገር ፎቶውም በየቦታው እየተገለጸ ለሕዝብ እንደሚታይ እግዚአብሔር ወልድም ከመወለዱ በፊት የተነገሩት ትንቢቶች የተመሰሉት ምሳሌዎች በርከት ያሉናቸው እነርሱም የመምጣቱን ዜና የሚያበስሩ ናቸው በመሠረቱ ለአምላክ ወደ ዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም እንዲወለድና ተወልዶም ቀስ በቀስ ካደገ በኋላ በመልዕልተ መስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት ያደረገው ምንድን ነው ? ለዚህ ምክንያት የሆነው የአዳምና የሔዋን በደል ነው ።

እግዚአብሔር መፍጠር የጀመረው በዕለተ እሁድ ሲሆን የፈጸመው ደግሞ በዕለተ ዓርብ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል በፍጥረታቱም መደምደሚያ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ለመላው ፍጥረት የበላይ አድርጎ በልጅነት አክብሮ በምድረ ገነት አስቀመጣቸው ሲያስቀምጣቸውም በምድረ ገነት ከሚገኙት የእንጨት ፍሬዎች መካከል የአንዲን ፍሬ ብቻ እንዳይበሉ ፣ ተደፋፍረው ቢበሉ ግን የሞት ሞትን እንደሚሞቱ አስጠንቅቋቸው ነበር ።

እነርሱ ግን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ትእዛዝ አክብረው ለመኖር አልቻሉም እንዳይነኩ የተከለከሉትን የእንጨት ፍሬ ቀጥፈው ተመገቡ በዚያ ጊዜ እንዲኖሩበት ከተፈቀደላቸውም ምድረ ገነት እየተገፉ እየተደፉ ወጡ ያለ ምንም ችግር ይኖሩ የነበር መራብ መጠማት መራቆት ደረሰባቸው ።

ሆኖም አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ተፈጥረዋልና የማወቅና የመመራመር ችሎታ ስለነበራቸው በፈታሒነቱ አንፃር መሐሪነቱ እንዳለ ተገንዘቡና ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ እግዚአብሔር ም መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የቀረበ ስለሆነ ኃዘናቸውንና ልቅሶቸውን ሰምቶ ከልጅ ልጆቸው ተወልዶ እንደሚያድናቸው ተስፋ ሰጣቸው የተስፋውም ምልክት "እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትነክሳለህ" የሚለው ቃል ነው ዘፍ 3፥15 ይህም በቀሌምንጦስ "አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ መቼ አድንኃለሁ" ለሚለው ትንቢታዊ ቃል መሠረት ነው በተጠቀሰው ምዕራፍ ቁ. ሀያ ሁለት "እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ መልካሙንና ክፉውን የሚያውቅ" በማለት ከሦስቱ አካላት አንደኛው የሰውን ሥጋ ለብሶ እንደሚወለድ ተነግሯል ።

እንዲሁም ወልደ እግዚአብሔር ከአብርሃም ዘር ተወልዶ የዓለምን ሕዝብ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የነበሩትንና ወደፊትም የሚኖሙትን በጠቅላላው እንደሚያድናቸው አውቆ ሲናገር በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ሲል ክርስቶስ ከአብርሃም ዘር የሚወለድ መሆኑን ተናግሯል ። ዘፍ 12፥3

በለዓም የተባለ አንድ ሀብተ መርገም የተሰጠው ሰውም ስለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን ተገልጾለት ትንቢት ሲናገር "ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምእሥራኤል" ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል ኃጢአትም ከእስራኤል ይወገዳል ብሏል ዘኍል 24፥17

ክቡር ዳዊት ስለቤተ መቅደስ አሠራር ለመጠየቅ ሱባኤ ቢገባ የአምላክ ሰው መሆንና ሥጋ መልበስ ተገለጸለት እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው" ሲል ትንቢት ተናግሯል መዝ 131.6

ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሰባተኛው ዓ.ዓ. ገደማ ተነሥቶ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ አምላክ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ቀስ በቀስ ካደገ በኋላ ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአትና በደል ተላልፎ የሰውን ልጅ ነፃ ማውጣት ሰፋ አድርጎ ትንቢት ተናግሯል ነቢዩ ከተናገራቸውም ትንቢቶች ጥቂቶችን እንመለከታቸዋለን ።

"እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ። ሕፃን ተወልዶልናል ፣ ወልድ ልጅም ተሰጠን አለቅነቱ በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ ተብሎ ይጠራል ፣ መካርም ብርቱም አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ መንግሥቱ ይበዛል ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ ይኖራል በትር ከዕሴይ ይወጣል ከሥሩም አበባ ይወጣል ብሏል ። ትን ኢሳ. 7.14፥9.7 ፣ 11 ፣ 11. ይኸው ነቢይ ስለሰው ልጆች የተቀበለውን መከራ በገለጸበት ምዕ 53 ቁ. 8



www.ethiopianorthodox.org

ላይ “ በማስጨነቅ በፍርድ ተወስዶ ስለሕዝቡ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረገ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆና ም ግፍን አላደረገም ነበር በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር” ይላል ።

ነቢዩ ኤርምያስም “እርሱም ራሱ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ወደዚህ ዓለም ይገባል እርሱ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው እርሱ አብሯቸው ይታይ ዘንድ ይገልጥላቸውም ዘንድ እሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለእርሱ አገልጋዮች ሊሆኑ መርጧል ለማስተማር ወደ ደብረ ዘይት ይወርዳል የተራበችንም ሰውነት ሁሉ ይመግባል ሲል ተናግሯል ሰቆ.ኤር 11 52

ከደቂቀ ነቢያት ሚክያስ “የኤፍራታ ክፍል የምትሆኝ አንች ቤተ ልሔም የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው ቦታዎች ብትበልጭ እንጂ አታንሽም ከአንቺ ወገኖች እሥራኤልን የሚጠብቃቸው ክርስቶስ ይወጣልና” ብሏል ትንሚክ 5.2 ነቢዩ ዕንባቆም “በሁለት እንስሶች መካከል አየሁህ” በማለት ተናግሯል ይህም የሚያስረዳው በላሞች በረት በተወለደ ጊዜ አህያና ላም እስትንፋሳቸውን መገበራቸውን ነው ይህንኑ በተጨማሪ ሲያረጋግጥ ነቢዩ ኢሳይያስ አህያ መንከባለያውን ላም ም የገዛውን ያውቃል” ብሏል ኢሳ 1.3

ሐዋርያው ጳውሎስ “ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በብዙ ኅብረ ትንቢት በብዙ ኅብረ አምሳል ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ ብሎ እንደገለጸው ከተነገሩት ትንቢቶች ጥቂቶቹ ተጠቅሰዋል። ኅብረ አምሳል የተባሉት ደግሞ ለሙሴ በአምሳል ነበልባልና ሐመልማል ለሄኖክ በአምሳለ ፀአዳ ላህም ለዳንኤል በአምሳለ ዕብን ቅውም ለዕዝራ በአምሳለ አንበሳ መፍርህ ታይቷቸዋል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ስለ ክርስቶስ መወለድ የተነገሩትን ትንቢታት የተመሰሉትንም ምሳሌዎች የምታስታውስባቸው የተለዩ ቀናት አሏት እነርሱም ከልደት በፊት ያሉት አራት ሳምንታት ናቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ “ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ላከ ከድንግል ተወለደ ብሎ እንደተናገረው የተነገሩት ትንቢቶች ሲፈጸሙ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ተወልዷል ገላ 4፡4 ። ነቢያት የተናገሩትን የትንቢት ፍጻሜ ሳያዩ ከዘመኑ ሳይደርሱ በመናገር ብቻ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለዚህም “እነሆ እላችኋለሁ ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል አንድ ይዘራል አንድም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና ። እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ” በማለት ተናግሯል ዮሐ. 4፡36-38 ነቢያት ትንቢት ተናግረው ሥጋዌውን በዓይነ ሥጋ አለማየታቸውን አስረድቷል ። ሐዋርያት ግን ትንቢት ሳይናገሩ ሰው ሆኖ የተወለደውን አምላክ በዓይነ ሥጋ ማየታቸውንና በእደ ሥጋ መዳሰሳቸውን አስረድቷል ።

እኛም በነቢያት የተነገሩትን ትንቢታት በክርስቶስ መፈጸማቸውን በሐዋርያት ስብከት ተረድተን ወንጌልን ተቀብለን የክርስቶስን አዳኝነት እናምናለን ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

---

# ቅዱስ ገብርኤል

ከገጽ ፬ የዞረ

ፈሩ ፣ ረሐብተኞችን ለሚረዱ ወደ እግዚአብሔር ለሚጸልዩ ለቤተ ክርስቲያን መባዕ ለሚያቀርቡ ሁሉ ምጽዋታቸውና ጸሎታቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲደርስላቸው የሚናገር ቅዱስ ገብርኤል ነው ስለዚህ አማኝ የሆነ ሁሉ በተቻለው መጠን ለችግረኛ ወገኑ በጎ ሥራ ሊሠራ ይገባዋል ።

ቅዱስ ገብርኤል ሰማዕታትም ጻድቃንም በሚሰቃዩበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ተልኮ የሚረዳቸው እሱ ነው ለምሳሌ እነ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ እነ ቅዱስ ቂርቆስ ፣ እነ አካውህ ስለ ክርስቶስ አምላክነት በሚመሰክሩበትና ወንጌልን በሚያስተምሩበት ወቅት በጠቅላላው ሌሎችም ሰማዕታት ሁሉ ለአናብስት በተጣሉ ጊዜ እናብሱቱን ለማዶች የሚያደርግላቸው በነደደው እቶን እሳት ተጥለው በፈላ ውኃ ውስጥ ተጨምረው በሚሰቃዩበት ጊዜ እሳቱን እያቀዘቀዘ የሚያጠፋላቸው በመካከላቸው እየተገኘ የሚያጽናናቸው የሚያበረታታቸው ፣ የሚያደፋፍራቸውም እሱ እንደሆነ የያንዳንዳቸው ገድል ይመሰክራል ።

የቅዱስ ገብርኤል ሥራና ታሪክ ጊዜ አልወሰነውም አሁን ባለንበት በሐያኛው ክፍለ ዘመንም ቢሆን እንደገና እየታደሰና በላይ ባላዩ እየጨመረ ከመሄድ በቀር የቀነሰበት ጊዜ የለም ይህንም እውነት የሚያደርገው በየዓመቱ ታህሣሥ 19 ቀን የቅዱስ ገብርኤል ስም ብሚጠራባቸውና መታሰቢያው በተቋቋመባቸው አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ተሳላሚዎች በብዛት ሲጎርፉ ይታያሉ በይበልጥም በቁልቢ ገብርኤል በርከት የለ ህዝብ ይታይበታል ከተሳላሚው መካከል አብዛኛው የሆነለትን የደረሰለትን ሲመሰክር መስማት በጣም ያስደንቃል ።

ከሚሰጠው ምስክር አንዳንዱ በመጠጥ አመል ተለክፌ ወፈፌ ሰካራም ሆኜ በወዳጅ በዘመድ ዘንድ ተጠልቼ ቤተሰቦቼ አባረውኝ ነበር አሁን ግን ቅዱስ ገብርኤል ከዚህ መጥፎ ጠባይ ገላግሎኝ ጥሩ ሰው ሆኜአለሁ የጠሉኝ ሁሉ ታርቀውኛል ሥራም አግኝቻለሁ እያለ ደስታውን ሲገልጽ ተሳላሚው ሁሉ እየሰማ የቅዱስ ገብርኤልን ታሪክ ያደንቃል ።

ሌላው ደግሞ በሲጃራ አመል ተይዤ ገንዘቤን ብቻ ሳይሆን ሰውነቴን ሁሉ ጨርሼ ገንዘብ አልበቃኝ እያለ እኔም ቤተሰቤም እንቸገር ነበር ። የሳል በሽ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# ጤነኛና ጥሩ ዜጋን ለማፍራት ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት ማሳደግ ይገባቸዋል ?

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው ። ወላጆች ልጆችን በማሳደግ በኩል በጣም ከባድ የሆነ ጥንቃቄ መውሰድ አለባቸው ። ልጆች ካላቸው የአእምሮ እድገት አንጻር ስንመለከታቸው መልካሙንና መጥፎውን ለመለየት የማይችሉ ነገር ግን ጎጅም ይሁን ጠቃሚ ያንን ካላገኙ የማይረኩ ናቸው ። ከዚህም ሌላ በአካባቢያቸው ካለው ዓለም ይልቅ ቤተሰቦቻቸውን በትልቅ ደረጃ ይመለከታሉ ። ይኸው ጠባያቸው በወላጆች ላይ የሚያዩትን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል ያስገድዳቸዋል ። ልጆች ወላጆች ጥልቅ የሆነ ፍቅር እንዲያሳኡአቸው ከባድ ፍላጎት አላቸው።

የአእምሮ ጥናት ትምህርት ልጆችን በፍቅር አለማሳደግ በልጆች የወደፊት ሕይወት ላይ ልዩ ልዩ ችግሮችን እንደሚያስከትል በሰፊው ያስረዳል ። ወላጆች ምንም አይነት የወላጅ ፍቅር ሳያሳዩ የሚያሳድጓቸው ልጆች ካደጉ በኋላ በጣም ጨካኞች ሌቦች ቀማኞች ራስን ወዳጆች ስለሌሎች የማይገዳቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሲኖሩም ከሰዎች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት መፍጠር የማይችሉና እንዲሁም ሌሎች ኅብረተሰቡን የሚጎዱ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ይሆናሉ ። ከዚህም ሌላ ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚወጣው ማንኛውም ዓይነት ሕግ ሊቆጣጠራቸውና ከነርሱ በላይ ሊሆን እንደማይችል የሚያምኑ ይሆናሉ ። በዚህም ምክንያት ፀረ ማኅበራዊ ኑሮ በመባል ይታወቃሉ ።

ልጆች ከአካባቢያቸው ከወላጆቻቸውና ከጓደኞቻቸው መልካምም ሆነ መጥፎ ነገርን መማር ይችላሉ ነገር ግን የአእምሮአቸው የእድገት ደረጃ የሚጎዳውን ከሚጠቅመው ለመለየት ስለማያስችላቸው ሁሉም ጠቃሚ ይመስላቸውና ያንኑ ይዘው ሊያድጉ ይችላሉ ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ወላጆች ከባድ ሃላፊነት አለባቸው መጥፎውን በመተው መልካሙን እንዲማሩ ጥንቃቄ የተመላው መመሪያ ሊሰጡአቸው ይገባል ።

በሌላ በኩል ወላጆች በልጆች ላይ በጣም የበዛ ቁጥጥር በማድረግ ነፃነት ተሰምቷቸው በጥሩ ሁኔታ እንዳያድጉ በልጆቹ የእድገት ደረጃ ላይ ከባድ የሆነ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ። ይህም በሕፃንነታቸው ብቻ ሳይሆን ካደጉ በኋላም የሚታዩ ልዩ ልዩ የአስተሳሰብም ሆነ የአሠራር ጉድለቶችን በሰውነት ላይ ያስከትላሉ። ለምሳሌ፦ ልጆች በእድገት ደረጃቸው ውስጥ አልፎ አልፎ በአልጋ ላይ ይሸናሉ በዚህ ጊዜ ወላጆች ይህ ሁሉም ሕፃናት የሚያልፉበት የእድገት ደረጃ መሆኑን ተገንዝበው ዝም ማለት አለባቸው ። ወይም ደግሞ የልጆችን የእድገትና የመቀበል ደረጃ በመመልከት ሥነ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ቀስ ብለው እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ማስተማር ይገባቸዋል ። ነገር ግን አንዳንድ ወላጆች ይህን ካለመገንዘብ የተነሳ ሕፃናት በዚህ ደረጃቸው ላይ እንዳሉ ባልጋ ላይ መሽናት እንደሌለባቸው ቁጣና ግርፋት እንዲሁም ከባድ ማስጠንቀቂያ ይሰጡአቸዋል ። ይህ በእውነቱ በልጆቹ ላይ ከባድ የአእምሮ ችግር ይፈጥርባቸውና ሊቆጣጠሩት ቀርቶ በመቀጠል ካደጉ በኋላም ነገሩ ሊሆንባቸው ይችላል ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው የአንጎል ክፍል የእድገት ደረጃው ገና በመሆኑ ነው ። ለዚህ ነው አንዳንድ ሰዎች ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ “ ልጄ ሌሊት በአልጋ ላይ እየሸና አስቸገረኝ” በማለት በሽታ መስሏቸው ሲያማክሩ ነገሩ ቀላል ነው ብዙ ሳትቆጣጠሩ አይታችሁ እንዳላያችሁ ዝም ብትሉት ይተዋል” የሚል ምክር የሚሰጣቸው ። ሌላም የዚሁ ተመሳሳይ አንዳንድ ሕፃናት ሲያድጉ ብልታቸውንና አካባቢውን የመያዝ ልምድ ይኖራቸዋል በዚህ ጊዜ ወላጆች በተለይም ከእንግዳ ፊት ይዘው ሲታዩ በጣም አሳፋሪ ሆኖ ስለሚታያቸው ይህን ነገር እንዲተው ልጆቹን አጥብቀው ያስጨንቋቸዋል ። ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ለመቆጣጠርም ሆነ መጥፎውን ለመለየት የሚያስችላቸው የአንጎል ክፍል ስላላደገ መተው በማይችሉበት ደረጃ የወላጆቻቸው ቁጣ በልጆቹ ላይ ከባድ የሆነ ውስጣዊ ጭንቀትን ይፈጥርና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊተውት ሲችሉ ነገሩ በመቀጠል ካደጉም በኋላ የመያዝ ልምድ ይኖራቸዋል ።

በተቻለ መጠን ልጆች የፈለጉትን ነገር በጊዜው መሟላት ተገቢ ነው ያለዚያ ልጆች እንደ ማንኛውም ሰው ውስጣዊ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መግታት ስለማይችሉ የፈለጉትን ካላገኙ ያዝናሉ ይተክዛሉ እንደዚሁም ይበሳጫሉ ። ይህ ብስጭትና ጭንቀት በልጆች ላይ ከተደጋገመ ራሳቸውን ከሁኔታዎች ጋር የማለማመድ ችሎታ ስለሌላቸው ልዩ ልዩ የአእምሮ በሽታዎችን ያስከትሉባቸዋል ። ስለዚህ ወላጆች የልጆችን ፍላጎት እንደቀላል ነገር መመልከት የለባቸውም ።

የልጆች ሳይኮሎጂካዊ ( ሥነ ልቡናዊ) ሁኔታ ውስጣዊ ስሜታቸውንና ጭንቀታቸውን ለተወሰነ ጊዜ ይዘው ለማቆየት እንደማያስችላቸው ተመልክተናል ለምሳሌ ፡- አንድ ሰው ረሀብን ተቆጣጥሮ ሊቆይ የሚችለውን ያህል ጊዜ አንድ ሕፃን መታገስ አይችልም ። ለብዙ ጊዜ እንዲቆይ ቢደረግ ግን ሕፃኑ ብዙ ተርቦ ከበላ በኋላ ከባድ የሆነ የአንጀት መታወክ ይደርስበታል ያቅለሸልሸዋል ያስታውከዋል ። ይህም ለህፃኑ ጤንነት መጥፎ ስለሆነ ወላጆች ይህን በመገንዘብ ለልጆች ምግባቸውን በሰዓቱ መስጠት አለባቸው ።

በገጽ ፲፫ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

## «ደግ ልጅ ስጠኝ»

አንዳንድ ሰዎች በዚህ ዓለም ብዙ ተባዙ በሚለው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ሚስት አግብተው ትዳርንም መሥርተውና ተደራጅተው ሲኖሩ እንደ አጋጣሚ ልጅ ያጡ እንደሆነ በተክሊልና በቃል ኪዳን ያገቡዋትን የሕግ ሚስታቸውን ያረቀች ሰነፎች በዚች ምክንያት ያለ ዘር ቀረሁ በማለት በብዙ ድካም የተሠራ ቤታቸውን ያፈርሳሉ ያለውን ንብረታቸውን ም በከንቱ ይበትናሉ ቤታቸውን አፍርሰው ባይሔዱ እንኳን በቤታቸው ሰላም አይኖራቸውም ጥዋትና ማታ ያለ ልጅ አስቀረሽኝ አስቀረሽኝ በማለት ይጨቃጨቃሉ በሕግ ከተጋቡ በኋላ ለብዙ ዘመን ልጅ ሳይወልዱ በኖሩት በጸጋዘአብና በእግዚእሐረያ መካከል ይህ ዓይነት ድርጊት አይታይባቸውም ነበር።

ይሁን እንጂ ጸጋ ዘአብና እግዚእሐረያ በመንፈሳዊ ፍቅር ተሳሥረውና በሰላማዊ ኑሮ ሲኖሩ የጓደኞቻቸው ማረፊያ የልባቸው ተስፋ የሚሆን ልጅ ባለመውለዳቸው ከባድ ሐዘን ይሰማቸው ነበር። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው አጥብቀው እግዚአብሔርን በጸሎት ከመጠየቅ ያቋረጡበት ጊዜ ከቶ አልነበረም ጸጋ ዘአብና እግዚእሐረያ በጾምና በጸሎት ተወስነው እንግዳን በመቀበል የተራበውን በማብላት የተጠማውን በማጠጣት የታረዘውን በማልበስ በጠቅላላ ክርስቲያናዊ ተግባርን በመፈጸም ረጅም ጊዜ ኖረዋል።

እግዚእሐረያ ዘወትር የምትጸልየው ጸሎት እንደዚህ ነበር « መላእክትንና ሊቃነ መላእክትን የፈጠርክ አንተ ነህ ያዘኑትን የምታረጋጋና የምታጽናና ሐዘናቸውንም ከልባቸው የምታስወግድላቸው አንተ መሆንህን አምናለሁ ስለ ዚህ ጌታ ሆይ በጌትነትህ ጽናትና በአምላክነትህ ከሃሊነት ልመናየን ተቀበለኝ አቤቱ ታዳጊ ቸል አትበል አንተን የሚያገለግል አንድ ደግ ልጅ ስጠኝ ብዬ ስለምንህ አንተን ደስ የሚያሰኝና በቅና መንፈስ የሚከተልህን እንጂ ከሕግህ የሚወጣ ትእዛዝህን የሚተላለፍ ከሆነ አለመወለዱን እመርጣለሁ» ወልድ እኩይ ያጸእል አባሁ ወእሞ ክፉ ልጅ አባቱንና እናቱን ሲያሳድብ ይኖራል ። ተብሎ እንደተጻፈ ሁሉ ክፉ ልጅ ራሱ ከመረገሙና ከመሰደቡም በላይ ወላጆቹም በእሱ ምክንያት ሲረገሙና ሲሰደቡ ይኖራሉ የሚል ጽሑፍ ስላለ የምትፈልገውን ልጅ ለይታ ለመነች።

እግዚእሐረያ ጸሎትዋን ፈጽማ ወደ ቤትዋ ከተመለሰች በኋላ ጸጋ ዘአብን እንዲህ አለችው ይህ ሀብታችን ተትረፍርፎ ታየዋለህ እናት አባት ይረዱበታል እንዳይባል አባትህና እናትህ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ለልጅ ይሆናል እንዳይባል ልጅ የለንም እንዲህ ከሆነ ይህን የተሰበሰበውን ወርቅና ብር በሕይወተ ሥጋ ሳለን ሥፍራ ሥፍራውን ብናስይዘው የተሻለ ነው ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን ለቤተ ክርስቲያን እንስጠው ለችግረኞች የሚሆነውንም ደግሞ ለችግረኞች እንመጽውተው ወርቅ ብር በሳጥን ተቆልፎ ከኖረ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስወቅሳልና ስትል በልብዋ የተሰማትን ሐሳብ አቀረበችለት ። ጸጋዘአብም ይህን ሐሳብ ከእግዚእሐረያ ቃል ሲሰማ በልቡ ያለውን ሐሳብ ስለ ነገረችው በታላቅ ደስታ ተዋጠና ሐሳብዋን ለማጽናት ያቀረብሽው ሐሳብ መልካም ነው በልቤም ያለው ነው ነገር ግን "ለመስጠት አትቸኩል፤- ከሰጠህ በኋላ ደግሞ አትጠራጠር" የሚል ጽሑፍ አለና ብንታገስ የተሻለ ነው አላት ጸጋ ዘአብ እንዲህ ማለቱ ለመመጽወት ፈቃዱ ያልሆነና ደስ ያላሰኘው ሁኖ ሳይሆን ቁርጥ ሐሳብዋን ለማወቅ ነበር።

ነገሩ በዚህ አልቀረም ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ በየመንገዱና በየቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ለወደቁ ችግረኞች ሰጧቸው ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውንም ንዋያተ ቅድሳት ባለቀባቸው አብያተ ክርስቲያናት መጸወቱ።

እንዲህ ባለ ሁኔታ ሲኖሩ በጸጋ ዘአብና በእግዚእሐረያ አንድ ከባድ ፈተና ደረሰባቸው ይኸውም በጣዖት የሚያመልክ መተሉሚ የሚባል ዓላዊ ተነሥቶ አብያተ ክርስቲያናትን እያቃጠለ ክርስቲያኖችንም እያሳደደ ጸጋ ዘአብና እግዚእሐረያ ካሉበት ቦታ ድረስ በዚህ ጊዜ የመተሉሚ መልእክተኞች እግዚእሐረያን አግኝተው መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች መልከ መልካም ሴት ስለነበረች ለመተሉሚ ሚስት ትሆናለች በማለት ማርከው ሲወስዷት ጸጋ ዘአብ ግን ሳይማረክ ቀረ ይሁን

እንጂ እግዚእሐረያንም ቢሆን ማርከው ይውሰዷት እንጂ ሐሳባቸው ሊፈጸምላቸው አልቻለም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በእግዚአብሔር ታዞ በቅርብ ሆኖ ይጠብቃት ነበርና።

እግዚእሐረያም ተማርካ ከሄደች በኋላ ጽኑ እምነት ስለነበራት ፈጽማ ሳትደነግጥ ሳራን ከጌራራ ንጉሥ ዳንኤልንም ከአናብስት አፍ ሶስናንም ከረበናት እጅ ያዳንክ አንተ ነህ እኔንም ከዚህ ዓላዊ እንደምታድነኝ እታመናለሁ እያለች ሳታቋርጥ ትጸልይ ነበር እምነው የሚጸልዩት ጸሎት ግዳጅ ይፈጽማልና አንድ ቀን መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከዚያ ነጥቆ ወስዶ ጸጋ ዘአብ ወዳለበት ሀገርና እሱ ወደሚጸልይበት ቤተ ክርስቲያን አደረሳት ጸጋ ዘአብም ቄስ እንደመሆኑ መጠን ቤተክርስቲያን ሲያጥን ቆይቶ ቢወጣ ከእግዚእሐረያ ከተለያዩ ከብዙ ወራቶች በኋላ ተገናኝተው መንፈሳዊ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንዴት ተማርካ እንደሄደች እንዴትም እንደተመለሰች አንድ ባንድ አስረዳችው ከዚህ በኋላ ባንድነት ሁነው እንደፊተኛው ኑሮአቸው በጾምና በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ እግዚአብሔር የልባቸውን የምህ

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል



# ትምህርተ ግዕዝ

## አመልካች መጠይቃን መራህያን

ተውላጠ ስሞች

አመልካች መራህያን

| ዘቅሩብ | የቅርብ |
|---|---|
| ዝንቱ (ዝ) | ይህ |
| ዛቲ (ዛ) | ይህች |
| እሉ እሉንቱ (ተባ) | እኒህ |
| እላ እላንቱ አን | » |
| **ዘርኁቅ** | **የሩቅ** |
| ዝኩ (ዝክቱ) | ያ |
| እንታክቲ (እንትኩ) | ያች |
| እልክቱ (ተባ) | እኒያ |
| እልክቶን አን | » |

መጠይቃን መራህያን

| | |
|---|---|
| ምንት | ምን |
| አይ | » |
| መኑ | ማን |
| ወ | አጣማሪ |
| እለ መኑ | እነማን |

ከዚህ በላይ በተነገሩት መራህያን ዓረፍተ ነገር ለመሥራት የሚከተሉትን ቃላት ማጥናት ያስፈልጋል ።

ነጠላ

| | |
|---|---|
| ወሬዛ (ተባ) | ወጣት |
| ድንግል | ልጃገረድ |
| ወለት | ሴት ልጅ |
| ወልድ | ወንድ ልጅ |

ብዙ

| | |
|---|---|
| ወራዙት | ወጣቶች |
| ደናግል | ልጃገረዶች |
| አዋልድ | ሴቶች ልጆች |
| ውሉድ | ወንዶች ልጆች |

## ዓረፍተ ነገር

| | |
|---|---|
| ምንት ውእቱ ዝንቱ፣ | ይህ ምንድን ነው ? |
| ዝንቱ ውእቱ ወሬዛ | ይህ ወጣት ነው |
| ምንት ይእቲ ዛቲ | ይህች ምንድን ናት ? |
| ዛቲ ይእቲ ድንግል | ይህች ልጃገረድ ናት |
| ምንት እሙንቱ እሉ? (ተባ) | እኒህ ምንድን ናቸው ? |
| እሉ እሙንቱ ወራዙት | እኒህ ወጣቶች ናቸው |
| ምንት እማንቱ እላ ? (አን) | እኒህ ምንድን ናቸው ? |
| እላ እማንቱ ደናግል | እኒህ ልጃገረዶች ናቸው |
| ምንት ውእቱ ዝኩ | ያ ምንድን ነው ? |
| ዝኩ ውእቱ ወልድ | ያ ወንድ ልጅ ነው |
| ምንት ይእቲ እንታክቲ | ያች ምንድን ናት |
| እንታክቲ ይእቲ ወለት | ያች ሴት ልጅ ናት |
| ምንት እሙንቱ እልክቱ (ተባ) | እኒያ ምንድን ናቸው ? |
| እልክቱ እሙንቱ ውሉድ | እኒያ ልጆች ናቸው |
| ምንት እማቱ እልክቶን (አን) | እኒያ ምንድን ናቸው ? |
| እልክቶን እማንቱ አዋልድ (አን) | እኒያ ሴቶች ልጆች ናቸው |
| መኑ ውእቱ ዝንቱ ? | ይህ ማን ነው ? |
| ዝንቱ ውእቱ ዮሐንስ | ይህ ዮሐንስ ነው ። |
| መኑ ይእቲ ዛቲ ? | = ይህች ማን ናት ? |
| ዛቲ ይእቲ ሠናይት | = ይህች ሠናይት ናት |
| እለ መኑ እሙንቱ እሉ? (ተባ) | = እኒህ እነማን ናቸው ? |
| እሉ እሙንቱ ዮሐንስ ወመኮንን | = እኒህ ዮሐንስና መኮንን ናቸው |
| እለ መኑ እማንቱ እላ (አን) | = እኒህ እነማን ናቸው |
| እላ እማንቱ ሠናይት ወአስቴር | = እኒህ ሠናይትና አስቴር ናቸው |
| መኑ ውእቱ ዝኩ | = ያ ማን ነው ? |
| ዝኩ ውእቱ መኮንን | = ያ መኮንን ነው |
| መኑ ይእቲ እንታክቲ | = ያች ማን ናት ? |
| እንታክቲ ይእቲ ኂሩት | = ያች ኂሩት ናት |
| እለ መኑ እሙንቱ እልክቱ (ተባ) | = እነዚያ እነማን ናቸው ? |
| እልክቱ እሙንቱ ዮሐንስ ወተካ | = እነዚያ ዮሐንስና ተካ ናቸው |
| እለ መኑ እማንቱ እልክቶን (አን) | = እነዚያ እነማ ናቸው |
| እልክቶን እማንቱ ኂሩት ወሠናይት | እነዚያ ኂሩትና ሠናይት ናቸው ። |

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ሊል ሊያገባ ይችላል ወይ ?

ዲያቆን መዘገቡ አክሊሉ
ከመንበረ ሕይወት መድኃኔአለም
አቃቂ በሰቃ ሸዋ

● ዲያቆን መዘገቡ አክሊሉ ስለ ጥያቄዎ እናመሰግናለን ። በመሠረቱ በክርስትና እምነት ባል ሚስቱን ወይም ሚስት ባልዋን እንዲፈቱ አይፈቀድም ከሁለቱ አንዱ በዝሙት ነውር ካልተያዘ በቀር በፍች መለያየት ክልክል ነው ። ብትሞትበት ወይም ቢሞትባት ግን በሥጋ ወደሙ ማግባት ይቻላል ሚስቱ የሞተችበት ወንድ የሚያገባት ልጃገረድ ብትሆን ለእርስዋ ጸሎተ ተክሊል ለእርሱ ፍትሐት ዘወልድ ተጸልዮላቸው በስጋ ወደሙ ሊጋቡ እንደሚችሉ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳል ። ፍትሕ ሥጋዊ አንቀጽ 24፡906 በአንፃሩም ባልዋ የሞተባት ሴት የምታገባው ባል ድንግል ቢሆን ለእርሱ ጸሎተ ተክሊል ለእርስዋ ፍትሐት ዘወልድ ይፈጸማል ሕግ ለሁሉም እኩል ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

አለቃ ደስታ እሸቴ ከአባታቸው ከቀኛዝማች እሸቴ ድንገቱና ከእናታቸው ከወይዘሮ ጐንተ ብርሃን ኃይሉ በሸዋ ክፍለ ሀገር በመርሐቤቴ አውራጃ ኮራ በተባለ ቀበሌ ታኅሣሥ 24 ቀን 1869 ዓ.ም. ተወለዱ ።

ወላጅ አባታቸው ድንገቱ ሥልጣኖ በመባል በታሪክ ከታወቀውና ከመንዝ ወደ መርሐ ቤቴ ተዛውሮ መንበሮ የተባለውን ከወለደ በኋላ ኮራንና ኢይመቆን በማቅናት ከአያያዘው የትውልድ ሐረግ መካከል የበቀሉ መሆናቸውን የታሪክ ዘገባዎች ያረጋግጣሉ ።

እናታቸውም ስመ ጥሩዎች የነበሩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የነመምህር መቃርዮስ የነመምህር ዘሃይማኖት የነአለቃ ኃይሉና የነመምህር ወልደ ዮና ሐረገ ትውልድ ያላቸው ስለሆኑ የአለቃ ደስታ እሸቴ አባታቸውም ሆኑ እናታቸው ከሊቃውንት መካከል የተገኙ የሃይማኖት ፍሬዎች ናቸው ለማለት ይቻላል ።

አለቃ ደስታ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአባት እናታቸው ቤት በተለይ አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የግዕዝንና የአማርኛን ንባብ እንዲሁም ጽሕፈትን ጭምር በሚገባ ተማሩ ።

በዚህ የትምህርትና የዕድሜ ወቅት ሳሉም በዕኑዕ ታመው ከዳኑ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን እናታቸውን የሚጠጡት ወተት እንዲሰጧቸው ጠየቁ እናታቸውም ዛሬ ዓርብ የጾም ቀን ነው ከሕመምህም በእግዚአብሔር ቸርነት ድነሃል ፣ እስከዛሬ ስትጠጣ ቆይተሃል የዛሬውን ግን ለነፍስህ ተውላት አሏቸው ።

ይሁን እንጂ አለቃ የልጅነት ዕድሜያቸው ጭምር አስገድዷቸው ወተት ካልተሰጠኝ መሞቴ ነው እያሉ ስለጠየቁ ከምትክም ሙት የወለድኩት ሥጋህን ብቻ ሳይሆን ነፍስህን ጭምር ስለሆነ ለሥጋህ እንደምጨነቅ ለነፍስህም ማሰብ ይገባኛል ሲሉ እናትዬዋ አስገነዘቡዋቸው ፣ በዚህም ጊዜ አለቃ ደስታ ‘‘እኔ ስጠጣ ነፍሴ ትጠጣ የለምን? ሲሉ ስለመለሱ በልጅነት ወቅት በተነገረው በዚህ ኃይለ ቃል የሰሙት ሁሉ ተገረሙ ።

እናታቸው ግን አሁን ነፍስህ ለሥጋህ ታጠጣለች እንጂ ለራሷ ትጠጣም ፣ ነፍስህ ግን የምትጠጣው አንተ ስትሞት በኋላ በሰማይ ቤት በመሆኑ አሁኑኑ ቶሎ ቶሎ እየላክህ በሰማይ ቤት ይጠራቀምልህ ስለአሉዋቸው አለቃ ደስታ እስከ ሰማይ ድረስ ማን ይወስድልኛል? ሲሉ ጠየቁ ።

በዚህም ጊዜ እናትየዋ ማታ ማታ ለልምና የሚመጡ ችግረኞች ናቸው የሚወስዱልህ ብለው ካስረዱዋቸው በኋላ የዓርብና የረቡዕን ቀናት ወተት በተለየ ማጠራቀሚያ እያጠራቀሙ ችግረኞች ለልመና ሲመጡ ልጃቸውን ጠርተው ወተትህን ወደ ሰማይ ይዘውልህ የሚወጡት ሰዎች መጥተዋል ስጣቸው ብለው ይሰጡዋቸዋል ። ከዚህ ላይ እናትየዋ እህልህን በነዳያን ሆድ ላይ ዝራ’’ የተባለውን ቃል የተረዱ ይመስላል ።

አለቃ ደስታ ወተቱን ከእናታቸው እየተቀበሉ ከደጅ ቆመው ምጽዋትን ለሚጠባበቁት ሰዎች ሲሰጡ እግዚአብሔር ለቁም ነገር ያብቃህ የሚል በረከት ከተቀባዮቹ ይነገራቸዋል ፤ ይኸንን ሁኔታ የሚመለከቱት የጐረቤትና የአካባቢው ሕዝብም ልጃቸውን በዘዴ ገቢረ ሠናይን በሚያስተምሩት ወላጅ እናት ከፍተኛ አድናቆት ይሰማቸው ነበር ።

ሊቁ ጠቃሚ በሆነው በዚህ ዓይነቱ የእናታቸው ትምህርት በመመራት ላይ ሆነው ሳሉ ዓፄ ቴዎድሮስ ከሸዋ ሲመለሱ የጦር ሠራዊታቸው የመርሐ ቤቴን ሕዝብ ማረከ በዚያም ወቅት አባታቸው ቀኛዝማች እሸቴ አብረው ተማረኩ ። ደስታ እሸቴም ከአባታቸው ጋር ተማርከዋል ንጉሡ ጐሐ ጽዮን ደርሰው በፈረስ እንደሆኑ ምርኮኛውን እየጐበኙ ሲያልፉ “ሕዝቡ የማረክንኮ ይኸ ነው” እያለ ሲነጋገር ደስታ ሰምተው ወደ ዓፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን ዘርግተው እያ! ወዴት ትወስደናለህ? ብለው ስለተናገሩ ንጉሡም በሕፃናዊ ዕድሜ ይኸንን በመናገራቸው አዝነውና አድንቀው ጐጃም ክፍለ ሀገር ከመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ቀለብም በየወሩ እንዲከፈላቸው ወዲያውኑ ትእዛዝ አስተላለፉላቸውና በመጀመሪያ ቅኔን ከነአገባቡ በሚገባ አድርገው ዐወቁ ።

በዚህም አጋጣሚ በሽተኞችን ሊረዱ የሚችሉበትን “ውሽባ” የተባለውን የቂጥኝ በሽታ ብሔራዊ መድኃኒት ተከታትለው ከዕውቀቱ ባለሙያዎች ስለአጠኑ በዚሁ ሕመም የተያዙትን ሁሉ ለመርዳት ቻሉ ።

ይልቁንም አንድ የተለየ የውሽባ ቤት አሠርተው ሕመምተኞቹን ሳይጸየፉ በሕክምና ረገድ ያበረከቱት የርህራሄና የእርድና አስተዋጽኦ ከሕፃን አእምሮ አስተሳሰብ ይመነጫል ተብሎ የማይገመት እንደነበረ ይነገራል

ከዚህም በቀር ወሀ ዋናን የበትር አመካከትን በዚሁ በልጅነት ዕድሜያቸው ስለአጠኑ በብሔራዊ እስፖርት ሞያቸው ይመሰገኑበት ነበር ።

በኋላም ከአባታቸው ከቀኛዝማች እሸቴ ጋር ወደ ራስ ዳርጌ ቤት በሚሔዱበት ጊዜ ከልጅ ካሣ ኃይሉ በጣም የጠነከረ ወዳጅነት መሥርተው ነበረና በተጨማሪ በዚሁ ወቅት የጠብ መንጃ አተኳኰስንና የፈረስ ጉግሥን ፀወቁ።

ከዚህም ቀጥሎ ወላጅ አባታቸው ሸንኩርት ሚካኤል ደብር ሆነው እንዲማሩ አድርገው ፀዋትወ ዜማን ከነአቋቋሙ ከአለቃ ብርሃኔ ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ቅኔን ከነአገባቡ ከአለቃ ዮሐንስ ዘንድ ተምረው የዜማና የቅኔ ትምህርት ባለሙያ ሆኑ ።

(በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ)



አለቃ ደስታ ከሸንኩርት ሚካኤል ትምህርት ቤት ሳሉ ከየክፍላተ አገሩና አውራጃዎቹ ለትምህርት የተሰበሰቡትን ተማሪዎች ከራሳቸው እየመገቡ በልብስ ለታረዙትም እህቶቻቸውን በማስፈተል እያለበሱ ያደርጉት የነበረው የርህራሄ ተግባር በወንጌል በተነገረው ቃል ላይ የተመሠረተ ነበር ።

ይልቁንም ይኸንኑ ማኅበራዊ ዕቅድ በበለጠ ለማስፋፋት በነበራቸው ዓላማ የምግብና የልብስ ተርድኦ የሚለግሥ ማኅበር አቋቁመው የትምህርት ጓደኞቻቸውን ችግር በማቃለላቸው በጣም ተመስግነውበታል ከዚህም የተነሣ ተያይዞ በቆየው ልማድ በየመንደሩ እየተዘዋወሩ ልመና የሚያካሔዱ ተማሪዎች ቁጥር በመቀነሱና ተማሪዎቹ አንድ ወገን ሆነው ትምህርታቸውን ብቻ ይከታተሉ ስለነበረ ተማሪ ብርቅና ድንቅ እየሆነ ባለመሰልቸቱ “በዘመነ ደስታ፣ የተማሪ ልመና ተገታ’’ እየተባለ መተረቱን የጆሮ ብቻ ሳይሆን በዘመኑ የነበሩ የዓይን ምስክሮች ታሪኩን ጭምር ያረጋግጣሉ ።

በየሣምንቱ እሑድ ከዚያው ከሚማሩበት አቅራቢያ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ አድረው ከመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቻቸው ጋር ጃርሶ ከሚባለው አገር ከአባት እናታቸው ቤት ሲሔዱ በሃይማኖት በበጐ ምግባር የታወቁት ወላጆቻቸው ቀደም ብለው ተዘጋጅተው ከነጓደኞቻቸው በሚገባ አድርገው በመቀበል ያስተናግዱዋቸዋል አዳራቸው ከዚያው ይሆናል ።

አለቃ ደስታ ሰኞ ጧት ገና ጎሕ ሲቀድ ተነሥተው የሥራው ወቅት በሚያመለክተው መሠረት ለጉልጓሎ ለአረምም ሆነ ለአጨዳ በወላጆቻቸው የሥራ መስክ ላይ ከነጓደኞቻቸው ይሰለፋሉ ፣ መብልን ውድድ ሥራን ጥምድ እየተባለ የሚነገረውም ባህላዊ መፈክር በአለቃ ደስታ ዘንድ ዋጋ የሌለው መሆኑ በግልጽ ይነገር ነበር፣ ከምሳ በኋላም ሰኞ ወደማታ ከነተከታዮቻቸው ወደ ትምህርት ቤታቸው ይመለሳሉ ለትንሣኤ በዓል በዚያው በወላጆቻቸው ቤት ከሚያደርጉት የስምንት ቀን ዕረፍት በቀር በየበዓላቱ ሁሉ የሚፈጸሙት መርሐ ግብር ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ነበር ።

ተማሪዎች ከትምህርትና ጥናት ውጭ የሆነውን የሥራ ጊዜያቸውን በከንቱ እንዳያሳልፉና የሥራ ልምድ እንዲኖራቸው ለማበረታታት በነበራቸው ዕቅድም በቤታቸው አካባቢ የነበረውን የአባታቸውን ሰፊ ቦታ አከፋፍለው ጌሾ ፣ ሽንኩርት የልዩ ልዩ ቅመማቅመም እንዲተከሉ በምክር ያበረታቱ ነበር ።

አንዳንዶቹንም ሰሌን ወይም የሸንበቆ ገበታ እንዲሠሩ አድርገው በዚህ ዓይነቱ የሥራ እንቅስቃሴ የሚገኘው ገቢ ለጋርዮሽ ጥቅም ለማኅበሩ እንዲሆን ያደርጋሉ ።

አለቃ ደስታ በዋዛ ፈዛዛና በሥራ ፈትነት ጊዜን ለማሳለፍ የሚደረገው የሰነፎች ሥርዓት አልባ ባህል ፈጽሞ የማይዋጥላቸው በመሆኑ ሥራን ጠልቶ ለምግብ የሚሰለፈውን ተማሪ ትልቁን በምክር ትንንሹን በብትር የማለዘብና ፈር የማስያዝ ችሎታ ነበራቸው በአለቃ ደስታ ዘንድ ማንም ሰው ቢሆን ከዓቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ሲቸገር እርዳታ አይነፈገውም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ውስልትናን ሲከታተልም ምክር፣ እንዲያም ሲል ቅጣት አይዘልለውም።

የማንም ሰው ልጅ ቢሆን የማይገባ ሥራ ሲሠራ ካገኙት በአርጩሜ መትተው ወይም ቆንጥጠው ይህ ልጅ ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀባላችሁት ነውና እንዳይፈረድባችሁ ጠብቁት ምከሩት አስተምሩት ተላልፎም በድፍረት በሚያጠፋው ጥፋት ቅጡት ብለው ለወላጆቹ አስረክበው ወደ ተግባራቸው ይመለሳሉ ጠባዩ የማይታረም ልጅ ከተገኘም ወላጆቹ በጠባይ ማረሚያ ስልታቸው ወደ ታወቁት ወደ አለቃ ደስታ ዘንድ ይልኩትና የተወላገደውን ጠባዩን መልካም ጠባይ ይፈጥሩለት ነበር ።

ለሕፃናትማ ስማቸው ብቻ ማስፈራሪያ ሆኖ ወላጆች ልጆች የብልግና ሁኔታ ሲታይባቸው ለደስታ ነው ወስጄ የምሰጥህ እያሉ በስማቸው ብቻ ልጆቻቸውን ያሠለጥኑ እንደነበረ ይነገራል ።

አለቃ ደስታ እሸቴ ደፋር ፣ ቆራጥና ኃይለኛ እውነተኛ ቁጣና ትዕግሥት ጭካኔና ርኅራኄ የሚፈራረቁባቸው ነበሩ ይኸንንም የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ባሕርያቸው አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ እንደወቅቱ በሥራ ይተረጉሙት ስለነበር በሰው ሁሉ ዘንድ ባንድ በኩል ሲፈሩ በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ይወደዳሉ ።

አባት እናታቸውም እንኳ ወላጆች ሆነው ሳሉ እንደወለዷቸው አድርገው ለልጃቸው የሚያሳዩት የፍርሃትና የአክብሮት ስሜት በሁሉ ዘንድ የተደነቀ ነበር ፣ ከላይ እንደተመለከተውም በርህራሄያቸው ብዛት ብዙዎች ይገረሙበታል ።

ለማስረጃም ያህል ከዕለታት ባንድ ቀን ከሸንኩርት ሚካኤል በስተምሥራቅ በሚገኘው ከአቦ ጠበል ለመጠመቅ ሔደው ሳሉ የከብት እረኛ የሆነ ልጅ ከገደሉ አፋፍ ላይ ወድቆ የነብር ጐሬ እየተባለ ከሚጠራው አረህ ላይ አረፈ ፣ የልጁም ወላጅ እናት በልጅዋ ላይ የደረሰውን አደጋ እንደ ሰማች ልጄን የበሉት ነብሮች እኔንም ይብሉኝ እያለች ወደ ገደሉ ስትሮጥ አይተው እናትየዋን በሩጫ ተከትለው እንድትታገሥና ዝም እንድትል በቁጣ ጭምር ከገሠፁዋት በኋላ’’ በእግዚአብሔር ኃይል ልጅሽን አመጣዋለሁ ነብሮቹ እኔንም ከበሉኝ ያንጊዜ ከእናቴ ጋራ ሆናችሁ ለልጅሽም ለእኔም ታለቅሻላችሁ ብለው በመጥምተ ርእስ ወደ ገድሉ ለመውረድ ሲነሡ እንዳይሔዱ በግልግልና በልመና መልክ የቀረቡትን ጓደኞቻቸውን በጣም ተቆጥተውና ከእጃቸው አምልጠው ገሠገሡ ።

ከዚያም ሲደርሱ ለነብሮቹ መከላከያ ጋቢያቸውን በራሳቸው ጠምጥመውና በድግ ጠፍረው አስረው በገደሉ ልጁ በግምባሩ ወድቆ ብዙ ደም ሲፈሰው



www.ethiopianorthodox.org

ነብሮቹም ከቃጣ ወደ ቃጣ (ከቋጥኝ ወደ ቋጥኝ) እየተዛለሉ ሲቦርቁ ደረሱ አስፈሪዎቹንም ነብሮች እንዳላየ አይተው እንደኢምንት ቆጥረው በፍጹም ቀና ብለው ሳይመለከቱዋቸው ልጇን ከወደቀበት አንሥት በኃይል የሚወርደውን ም ደም ጠለንዥ በሚባለው ቅጠል አጥ ምተው እንዲቆም አደረጉት ፤ ከዚህም በኋላ ልጇን በትከሻቸው እንኮኮ ብለው ተሸከመውና ከገደሉ አውጥተው ለወላጅ እናቱ አስረከቡ በሕዝቡም ዘንድ የደስታ ልጅ እየተባለ እንደኖረ ይነገርላቸዋል ።

በርሳቸው አማካይነት በሽንኩርት ሚካኤል ይደረግ የነበረውንም መንፈሳዊ አገልግሎት በጣም ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ ቀጥሎ የተጻፈውን ቅኔ የተቀኙት በዚሁ ወቅት ነበር ።

መወድስ

ልደተ ምድራዊ አዳም እምነ ምድራዊ ፤ ልደተ መርዓቱስ ሔዋን እምገቦ አዳም እንታክቲ ።

ወእላ ግብራተ መንክራተ ዓለም ዛቲ፡ አብ ወእም ዘምስለ ምት ለሔዋን እንበለ አዳም አኮኑ አልባቲ ። ወለዘ እምአዳም ተወለድነ ኮነተነ እመ እንዘ እኅትነ ይእቲ ።

ልደተ አሐዱስ ሰማያዊ እምነ ምድራዊት አሐቲ ። መንክር ዘየዓቢ ወዘ ኢይትሐተት ለሐታቲ ቅድመ ልደቱ እምድር ዘበድንግልና ክልዔቲ እስመ ይወልደ ዘወለደ እንዘ መዋቲ ወኢመዋቲ

አማርኛው

የምድራዊ አዳም ልደት ከምድራዊ ሲሆን የሙሽራይቱ ሔዋን ልደትግን ከአዳምጎን ነው እነዚህም ሥራዎች የዓለም መደነቂያዎችናቸው ሲሔዋን፤ ከአዳም በቀር አባትና እናት የሏትምና ፤ ከአዳም ለተወለድን ለእኛም እህታችን ስትሆን እናታችን ናት ።

ከአንዲት ምድራዊት (ማርያም)ሰው የሆነው የአንዱ ሰማያዊ ክርስቶስ ልደት ግን የማይመረመርና የሚበልጥ የድንቅ ድንቅ ነው ከምድራዊ ልደቱ አስቀድሞ ሁለት በሆኑ ድንግልናዎቿ (በሥጋና በአሳብ) መዋቲና ኢመዋቲ የሆነው የወለደችው ልጅዋ ይፈጥራታልና።

## አለቃ ደስታ በትርጓሜ መጻሕፍት ቤቶች

ከላይ እንደተዘረዘረው ሁሉ አለቃ ደስታ ከትምህርት ጓደኞቻቸውና የፀዋትወ ዜማና የቅኔ ትምህርታቸውን አደላድለው ካወቁ በኋላ ለጥቂት ጊዜ በአባትና እናታቸው ቤት ቆይተው ሐዲሳትን ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ፤ ሊቃውንቱን ከአለቃ ኅሩይ ብሉያትን ከአባ ተድላ አጠናቅቀው ተምረውና ሊቅ የሚያሰኘውን ስም ተቀዳጅተው እንደገና ወደአባትና እናታቸው ዘንድ ሲመለሱ ወላጆቻቸውና ቤተዘመዶቻቸው ተሰብስበው ሚስት አግብተው ትዳራቸውን እንዲመሠርቱ ጠየቁዋቸው ።

ሊቁ ግን በሰው እጅ ያልታነፀውን ሰማያዊውን እንጂ የዚህን ዓለም ቤት ንብረት በፍጹም የማይፈልጉት መሆኑን ስለአረጋገጡላቸው የቆራጥነት ጠባያቸውን ያውቁታልና እግዚአብሔር እንደፈቀደለት ይሁን ብለው ጥያቄያቸውን ገቱ ።

ሊቁ አለቃ ደስታ ወደሌላ ክፍለ ሀገር ለመዛዋወር ዐቅደው ኖሮ ከአባት እናታቸው ቤት ተነሥተው እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር እንዳደሩ ሌሊቱን በጽኑዕ ሕመም ስለተያዙ ወደ ደብረ ሊባኖስ አድርሱኝ ብለው ዘመድ ወዳጅ በአልጋ ተሸክሞ ወሰዶዋቸው ውላላ ገባባ ከሚባለው ከደብረ ሊባኖስ አፋፍ ሲደርሱ በጣም በገኦ ሆነው ከአልጋ ወርደው እየተደገፉ በእግራቸው ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው ዕለቱን ጠበል ተጠምቀው አደሩ ጤናቸውም በጣም ተሻሻለና ዳኑ ።

ከዚህም በኋላ ወዳጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን እንግዲህ የውላገባባን አፋፍ ዘልቄ ለመሔድ የምችል አይመስለኝምና እናንተ ሒዱ ብለው ከዚያው ከገዳሙ ለመኖር የቤት ሥራ ጀመሩ ።

ቤታቸውም ዙሪያ ጓዳ ሆኖ ለአረጋውያንና ጠበል ለመጠበቅ ለሚሰበሰቡ ሕሙማን ማረፊያ መሆን እንደሚችል ሆኖ ተሠራ ፤ አለቃ ለዘወትር ቅዳሴ አስቀድሰው ጠበል ከተጠመቁ በኋላ ከቀኑ በ11 ሰዓት ከሁለትም ከሦስትም እንግዶች ጋር ሆነው ይመገቡ ነበር ።በቤታቸውም ጓዳ ያስተኙዋቸውን ሕሙማን መርዳት የዘወትር ሥራቸው ነበር ተከታይ እህታቸው መንነው በዚያው በገዳሙ ሴት ደብር ስለሚገኙ የሴት በሽተኛ ሲያጋጥማቸው በተማሪዎቻቸው እያሳዘሉ እንዲያስታምሟቸው ወደኒሁ እህታቸው ይልኩዋቸው ነበር ።በዚህም ወቅት ለብዙዎች ደቀ መዛሙርት የትምህርትን ፋና አብርተውላቸዋል ።

አለቃ ደስታ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በመማርና በማስተማር ብቻ ሳይወሰኑ ትምህርትን በሥነ ጽሑፍ ከትውልድ ወደትውልድ ማስተላለፍ የሚገባቸው መሆኑን ያምኑ ነበር ።

ከበስመ አብ እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ያለውን አጭር የዘወትር ጸሎት ከግእዝ ወደ አማርኛና ወደ ኦሮምኛ ተረጐሙ ። ቀጥሎም "ስምዕየ ማርያም" የሚለውን በወሮምኛው ሲተረጉሙ "ከመሰከርቱ ማራሚዳ" ካሉ በኋላ ለወሮምኛው ቋንቋ ዳ የማይመች ነው ብለው በፊደል ላይ እንደ ጰ በራሱ ላይ ሠረዝ አስቀመጡና ይኅንኑ ለሁሉም አስረዱ ።

ከዚያም ቀጥሎ ውዳሴ ማርያምን ቅዳሴ ማርያምን ፤ ይዌድስዋን ወበሣድስን ፤ ይቤላ መልአክን ኪዳንን ትምህርተ ኅቡዓትን ከውዳሴ አምላክ የባስልዮስንና የኤፍሬምን ድርሰት ከተአምረ ማርያም እስግድለኪን በነጠላ ትርጓሜ እንዲሁም ብዙዎችን የጸሎት መጻሕፍት ተረጐሙ ።

አንቀፀ ብርሃንን ግን በአንድምታ ትርጓሜ በሚገባ አድርገው አብራሩት የትርጉምና የጽሑፍ ተግባራቸውንም በመቀጠል አራቱን ወንጌላት ከነመቅድሙ ዳዊቱን እየተረጐሙ ጸፉት ዳዊቱንም ለጸሎት እንደሚመች አድርገው በ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የ .ሰጡበት ፤ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ለምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ

አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሳላምና ፀጋ ይብዛላችሁ ፤ ከዚህ ቀጥሎ ጥያቄዎች አሉኝና እንድትመልሱልኝ በተስፋ እጠባበቃለሁ ፤ ጥያቄዎቹም

1ኛ ጾም ማለት ለተወሰኑ ሰዓታት ወይም ቀናት ያለ ምግብና ያለመጠጥ መዋል ፤ ደግሞም ከሥጋና ከሚያሰክሩ ልዩ ልዩ መጠጦች ተከልክሎ በመራራ ኃዘን ፤ በጸሎትና በንስሐ የጾም ጊዜን ማሳለፍ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ።

እኔ ግን የአፍ ክርስቲያን በመሆኔ ከዚህ ተግባር ርቄ በዓለማዊ ተግባር ተስማርቼ ዓለማዊ ሥራዎችን በመፈጸም ላይ ነኝ። መጾሙን እጾማለሁ፤ ዳሩ ግን እውነተኛ ጾም አልጾምም፤ ለይምሰል ያህል ከሥጋ ፤ ከወተት ፤ ከቅቤ ፤ እጾማለሁ ፤ ነገር ግን ምርጥ ከሆኑ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች አልጾምም ። በቀን ሶስት ጊዜ እመገባለሁ ከጥዋት ጭምር ማለት ነው ።

ከተመቸኝ ከመጠጥ ዓይነቶች ምንም ሳይቀረኝ እጠጣለሁ ። በዝሙት በኩልም ከአየኋት ቆንጆ ጋር በምኞት አመነዝራለሁ ።

ታዲያ ከዚህ ሁሉ መጥፎ ተግባሬ ተመልሼ ፍጹም ክርስቲያን ለመሆን እመኛለሁ ፤ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ስሄድ እንደሰረቀ ሰው ፍርሃት ይይዘኛል የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቤት እንደ ይፈርኩ እየቆጠርኩ እቸገራለሁ ከዚህ ጭንቀት የሚያወጣኝ ማን ነው? ።

አቶ አብደታ ሆማ

አቶ አብደታ ሆማ ችግርዎን ተረድተናል ስለአንደኛው ጥያቄዎ በእርግጥም ጾም ማለት ለተወሰኑ ሰዓታት ወይም ቀናት ያለምግብና መጠጥ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን ከክፉ ነገር መወገድ ከመጥፎ ነገር መራቅ ጭምር ያስፈልጋል ። እውነተኛ ጾም ከራስ ፈቃድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያስፈጽማል ፤ ከራስ ይልቅ ለሌላው ያሳስባል ። በወንድሙ ላይ የሚያየውን ኃጢአት አይዘክርም ። ይህንን የሚፈጽም እውነተኛ ጿሚ እውነተኛ ክርስቲያን ይባላል በተረፈ በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን እንደነበሩት ጾዋሚያን ጾም የሚጾም ቢኖር ከወቀሳ አያመልጥም ። ነቢዩ ኢሳይያስ በነበረበት ዘመን የነበሩት አይሁድ ጾምን ያዘወትሩ ነበር ። ዳሩ ግን ጾማቸው የጽድቅ ጾም ሳይሆን ለልማድ ያህል ይጾሙ ነበር እንጂ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ የጽድቅ ጾምን አይጾሙም ነበር ። ስለዚህም እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ እንደሚከተለው ወቅሶ ጾማቸውን ነቅፎባቸዋል ። "ጽድቅን እንዳደረጉ ፤ የአምላካቸውንም ፍርድ እንዳልተው ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል ። ወደእግዚአብሔርም ለመቅረብ ይወዳሉ ።

ስለምን ጾምን አንተም አልተመለከትኸንም ። ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን አንተም አላወቅህምን? ይላሉ እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፤ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ ። እነሆ ለጥልና ለክርክር ትጦማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ ድምፃችሁንም ወደላይ ታሰሙ ዘንድ እንደምትጾሙት አትጾሙም እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን ? ሰውስ ራሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? ራሱን እንደእንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ፤ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን ? በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ ፤ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቁ ዘንድ ፤ የተገፉትንስ አርነት ትሰዱ ዘንድ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን " በማለት ማንም ሰው በሚጾምበት ጊዜ ማድረግ የሚገባውን ዘርዝሮ ያስረዳል ። ኢሳ 58፤ 1-14 ስለዚህ እርስዎም መጾም የሚገባዎ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ መሆን አለበት እንጂ እንዲያው ላይ ላዩን ለአፍ አዊ እጾ ማለሁ ማለቱ ጥቅም አይሰጥምና ያስቡበት እርስዎ በቀን ሶስት ጊዜ የሚመገቡ መሆንዎን ገልጠዋል ጥዋት ቁርስ በሰዓት ምሳ ፤ ማታ ራት መሆኑ ነው ። ታዲያ ጥዋት ቁርስ ከበሉ ምኑን ጾሙትና ነው እጾማለሁ የሚሉት? ጾም ማለት እኮ ለቁርስ ወይም ለምሳ የሚያደረጉትን ለነዳያን መስጠት ማለት ጭምር ነው ። ጾም ለተወሰነ ሰዓት የሚቆይበት ስለሆነ ጥዋት ከተበላ ጾም ጾምኩ ማለት አይቻልም ።

ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በሚያዘው መሠረት መጾም እንዳለብዎ



www.ethiopianorthodox.org

እንግርዎታለሁ ። በአትክልት በኩልም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን በምታዘው መሠረት መፈጸም እንዳሌብዎ አይዘን ጉት ስለዝሙት ጉዳይ አንስተዋል ይህ ም ክርስቲያኖች በጾምም ሆነ በሌላ ጊዜ ፈጽመው ሊከለክሉት የሚገባ ዐቢ ይ ነውር ነው የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ዓይን ክፉ ነገር ከማየት፣ጆሮ መ ጥፎ ነገር ከመስማት አፍም ክፉ ነገር ከመናገር ይጹም ይላል ። ይህም ከነቢዩ ኢሳይያስ ቃል ጋር የሚስማማ ስለሆነ እርስዎም ይህንኑ ተረድተው ከሁሉም ነገር መጾም አለብዎት እንጅ እንዲያው ከቅቤና ሥጋ መከልከል ብቻ እንደጾም ስለማይቆጠር ያስቡበት ።

ካሉበት ጨለማ የሚያወጣወትም እግዚአብሔር ስለሆነ እግዚአብሔርን ይመኑ እንጂ በሰው ተስፋ አያድርጉ ።

# ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ድጋሚ በነጠላ ትርጓሜ ተረጕሙት ለ ምን እንዲህ ይደክማሉ ቢሏቸውም በ ቃል ያለ ይረሳል ፣ በመጽሐፍ ያለይወ ረሳል ፣ የመምህራን እንደበት ይዘጋል የተማረ ልቡ ይሰንፋል በዚያም ጊዜ የ አባቶቻችን ትርጓሜ መጻሕፍት ይጠፋ ል እያሉ ያስረዱዋቸው ነበር ይባላል ፣ የዳዊቱ ነጠላ ትርጓሜና የአራቱ ወንጌ ላት ትርጓሜ ሦስተኛው ቅጅም ከ ቀራንዮ መድኃኔዓለም እንደነበረ ታው ቋል ።

ለራስ ካሣም ዲድስቅልያን ግር ይስ ሐቅን እየተረጐሙ ጽፈውላቸዋል አለ ቃ ደስታ ጥቂቶችን ደቀ መዛሙርት በ ቃል ከማስተማር ይልቅ ትምህርቱን ለ ብዙዎቹ ለሚያስተላልፈው ወረቀት ማ ቀበል ይሻላል በሚል መንፈስ ይመሩ ስለነበረ ከትምህርት ጉባኤ ይልቅ ወደ ሥነ ጽሑፍ ያደሉ ነበር ይባላል ።

እምስቱ አዕማደ ምሥጢርን ባጭሩ ጽፈው ሕፃናት እሑድ እሑድ እንዲያ ጠኑ አድርገው ነበርና አካላዊ ቃል ከአ ብ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ሰው ሆኖ ተወለደ ፣ ተሰቀለ ፣ ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በ ሦስተኛውም ቀን ተነሣ ከሚለው ላይ ፈታውራሪ ነቢየ ልዑል ተክለ ጻድቅ እንዴት ሊሆን ይቻላል? ሲሉ ላቀረቡት ጥያቄ ወልደ ሥላሴ ጎሩይ ቢሆን ነው እንጂ ባይሆንማ እንዴት ይነግሩናል ? በማለት መለሱላቸው ይባላል ።

አለቃ ደስታ ለተጠየቁት በተሎ መልስ የመስጠት ልዩ ስጦታ ነበራቸውና አን ድ ታላቅ ሰው ልጃቸውን ተጣልተው አ ስረውት ሳለ ልጁ ከአባቱ እንዲያስታ ርቁት ተፀፅቶ ምልጃቸውን ስለጠየቀ ዕርቅን ከአባቱ በጠየቀበት ጊዜ እግዚ አብሔርስ ዲያብሎስን አሥሮት ይኖር የለምን? አልፈታውም በማለት ከአባት የው ለቀረበላቸው መልስ ሊቁ እግዚአ ብሔር እኮ ዲያብሎስን አሥሮ ያኖረው ንስሐ ባለመግባቱ ነው ልጅዎ ተፀፅቷ ል ፣ ንስሐ ገብቷልና ይማሩት ስለአሏቸ ው በንግግራቸው ተደንቀው ልጃቸውን ከእሥራቱ ፈትተው ታርቀውታል ።

ከዕለታት ባንድ ቀን አንድ ሰው ሕ ልም እናያለን እንዲህ ይሆናል እንዲህ ይደረጋል እንደሚሉት አንዳንድ ሰዎች ገምቷቸው ኖሮ ስለዘመኑ ሁኔታ ምን ህልም ይታየዎታል? ብሎ ቢጠይቃቸ ው ይኸ ሁሉ የማየው ሕልም ነው ከማየ የውም ከብዙው ሕልም አንዱ ሕልም አንተ ነህ ትርጉሙን ግን የሚፈታው ጊዜ ነው ካሉት በኋላ በግጥም ። ምን ያስጠይቀናል የሚመጣ ወሬ ሲሔድ እያየነው እንደትላንት ዛሬ ብለው አስናበቱት ።

ካህናት በማኅሌት ውለው ወይም አድረው ቅዳሴ ሲገቡና ሲወጡ እንዲ ሁም አንዳንዶቹ ምእመናን ከሥጋውና ከደሙ ሲርቁ በማየታቸውም

ቆሞ አስቀድሶ ካልበሉ ከሥጋው ፣ ካልጠጡ ከደሙ
አሳርደው መሔድ ምንድን ይሆን ጥቅሙ ?
ንጉሥ ግብር ሠርቶ ተገኝቶ ባዳራሽ አይገርማችሁም ወይ ኑ ብሎ ቢላቸው ያሸከሮቹ መሸሽ

ብለው ጽፈው ለብዙዎቹ እንዳደሏቸው ይነገራል ። ውዳሴ እምላክን በግዕዝ ሲጸልዩ የነበሩ አንድ ሰው አለቃ ደስታ ወደአማርኛ የተረጐሙትን ቢልኩላቸው እስከዛሬ ድረስ የውዳሴ እምላክን ጥሬ ውን ስንጾ ነበር የምመገበው አሁን ግን ባለሞያው ሊቅ ዳቦ አድርጐ የላከልኝን እነሆ እመገባለሁ ብለዋል ።

ሊቁ ከግእዝ ወደአማርኛ ከመለሷቸው መጻሕፍት ፣ ቀሌምንጦስ ፣ ደቂቀ ነቢ ያት አሥራአራቱ ቅዳሴያት ፍትሐ ሥጋ ዊና ፍትሐ መንፈሳዊ የሚሰጥበት ፍት ሐ ነገሥት ተክሊል ግብረ ሐዋርያት ይ ገኙባቸዋል ።

አለቃ ደስታ እሸቱ ደዌነፍሱን ለመፈ ወስና ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስ ታረቅ በሚያደርጉት ጥረት አንፃር የሥጋ ደዌ ያለባቸውን ማለት በውርደኝነት ቁስል ፣ በቁስለ ሥጋ በቆላ ቁስል በሻህኝ በዕለት ቁስል በደም መፍሰስ በዓይን ሕመም የሚሠቃዩትን ሁሉ በብሔራዊ መድኃኒት እያከሙና ራሳቸው እያስታ መሙ በጸሎት ጭምር ፈውስ እንዲያገ ኙ ያደርጉ ነበር። የሚያደርጉትንም መ ድኃኒት ሁሉም እንዲጠቀምበት በግል ጽ ያስጠኑ ነበር በተስቦ በሽታ የታመ ሙትን ያለፍርሃት ማስታመም ሕመም ተኞን መጠየቅ የተጣሉትን ማስታረቅ የሞቱትን አጥቦና ገንዞ መኑበር የዘወ ትር ተግባራቸው ሆኖ ኖሯል ።

ከዚህም ሁሉ ጋር በባቡር የሚፈጨው እህል በሰይጣን ነው የሚለው ኋላ ቀር ባህል በገዘው ተቋቁመው በረብረ ሊባ ኖስ ገዳም በሴት ደብር የባቡር ወ ፍጮ ተቋቁሞ ገዳሙን እንዲረዳ አድርገዋል ።

መላ ሕይወታቸውን በትምህርት በማ ስተማር በሥነ ጽሑፍና በበጐ ተግባር ሲያስጌጡ የነበሩት አለቃ ደስታ እሸቱ አሥር ወር ያህል ከታመሙ በኋላ የካ ቲት 8 ቀን 1917 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ቀብራቸውም በደ ብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሞአል ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# ጤናችና ጥሩ ዜጋን...

ከገጽ ፯ የዞረ

ባጠቃላይ አስተዳደግን በሚመለከ ት ሁኔታሌሎች ብዙ ሐሳቦች ይኖራሉ፤ ስለዚህ ነገር የአእምሮ በሽታ ጥናት ሊቆ ች በሰፊው ያስረዳሉ። ከዚህ ላይ የምንረ ዳው ልጆችን በተገቢው መንገድ በጥሩ ፍቅር አለማሳደግ እንዲሁም አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ አብዝቶ መቆጣጠር ወ ይም መቅጣት በሚገባ ጊዜ ዝም ብሎ መመልከት በልጆች የወደፊት ሕይ ወት ውስጥ ልዩ ልዩ ጉድለቶች ወ ይም መጥፎ ጠባይ እንዲታይ ያደርጋ ል ። ምንም እንኳ አንዳንዶች ልጆች ከ አካባቢያቸውና ከጓደኞቻቸው አንዳን ድ ሁኔታወችን ቢማሩም ብዙዎቹ የሚ ያንጸባርቁት የቤተሰባቸውን ጠባይ ነ ው። በእናትና በአባታቸው መካከል ፍ ቅርና ሰላም የሚያዩ ከሆነ ያንኑ ጠባይ ይዘው ለማደግ ይሞክራሉ። በመጥፎና በሚጨቃጨቁ ቤተሰቦች ውስጥም ካደ ጉ እንደዚሁ ነው። ስለዚህ ልጆች መል ካም ጠባይ ይዘው እንዲያድጉ በእግዚአ ብሔር ቃል ልናንጻቸው ይገባል። በእ ድሜ ከኛ በማነሳቸው ልጆችን ልንንቃ ቸውና የሚጠይቁትንም ጥያቄ በማቃለ ል ለመጠየቅና ለማወቅ ያላቸውን ፍላጎ ት ማዳከም የለብንም። ለዚህ ነገር ክርስ ቶስ ለኛ ለክርስቲያኖች ትልቅ ምሳሌ ያችን ነው ። “ ሕፃናትን ወደኔ ይመ ጡ ዘንድ አትከልክሏቸው” በማለት በ ፍቅር ወደርሱ እንደጠራቸው እንመለ ከታለን ። የመልእክቱ ዋና አላማ ክርስ ቶስ ሕፃናትን ወደርሱ በማቅረብ ፍቅር ን እንዳሳያቸው ሁሉ ወላጆችም ይህንኑ የመሰለ ፍቅር ለልጆቻቸው ማሳየ ት እንዳለባቸው ለማሳሰብ ነው ። የወላጅ ፍቅር በማጣት የሚያድጉ ልጆ ች ምን ዓይነት አቋም እንደሚኖራቸው ተመልክተናል ። ስለዚህ ይህ ችግር በ ልጆቹ ሕይወት ላይ እንዳይፈጠርና ጥሩ ዜጎችንም ለማፍራት በፍቅርና በ ጥሩ ሞራል ማሳደግ ተገቢ ነው ።

ተማሪ ነርስ ልዕልት ረታ

# ቅዱስ ገብርኤል

ከ፮ኛው ገጽ የዞረ

ታም ይዞኝ ሰውነቴ ሁሉ መንምኖና ከ ስቶ ሲባን እመስል ነበር አሁን ግን ቅ ዱስ ገብርኤል ከእንዲህ ያለው መጥ ፎ ጠባይ ስላላቀቀኝ እዩት ሰውነቴን ወፍሮ እያለ ጡንቻውን ሲያሳይ መመ ልከት ደግሞ ሌላ ትርኢት ነው ።

ሴቶችም በበኩላቸው ይኸውላችሁ መካን ሆነን ስንኖር ይኸው ቅዱስ ገብ ርኤል ልጅ ሰጥቶን ልጆቻችንን አዝለ ን ክርስትና ልናስነሳ መጥተናል እልል በሉልን አጨብጭቡልን እያሉ ቤተ ክርስቲያኑን እያዞሩ በሕዝቡ ፊት ሲመ ሰክሩ መስማት ሌላው አስደናቂ ነገር ነው ።

ይህን የመሳሰለውን ታላቅ ሐይልና አስደናቂ ሥራ በየጊዜው የሚሠራው እግዚአብሔር በቅዱስ ገብርኤል አድሮ ስለሆነ እግዚአብሔርን እናመስግነው “የእግዚአብሔርን ሥራና በምድር ላይ ያደረገውን ተአምራት ታዩ ዘንድ ኑ” ተብሎ ተጽፎአልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ደግ ልጅ ስጠኝ

ከገጽ ፰ የዞረ

ት አይቶ ጸሎታቸውንም ሰምቶ ምጽ ዋታቸውንም ተቀብሎ ያን እግዚእሐረ ያን በቅርብ ይጠብቃት የነበረውን መ ልአክ ላከላቸው መልአኩም እግዚእ ሐረያ እንደምትፀንስና ደግ ልጅ እንደ ምትወልድ አበሰራት እግዚእሐረያም ባበሰራት ልክ በዘጠነኛው ወር ታኅሣሥ 24 ቀን 1197 ዓ.ም. አካባቢ ጻድቁ ተክ ለ ሃይማኖት ተወለዱ ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ ጊዜ ታላቅ ደስታ ሆነ ጸጋ ዘአብና እግ ዚእሐረያ ከሐዘናቸው ተጽናኑ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ልጅ በማጣታቸው ያዝኑ የነበሩት ሁሉ በደስታ ተዋጡ አቡነ ተ ክለ ሃይማኖት ሲወለዱ ብዙ አስደናቂ የሆኑ ሥራዎች ታይተዋል ከብዙዎቹ አንዱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በሦስተኛው ቀን እጃቸውን ወደላይ ዘርግተው አሐዱ አብ ቅዱስ ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ሲሉ እግዚአብሔርን ማመስገና ቸው ነው ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በልደታቸው ጊዜ ይህንን ቃል ሲናገሩ በአካባቢው የነበረው ሕዝብ በአንክሮና በተደሞ ይ መለከታቸው ነበር በተወለዱ በአርባኛ ውም ቀን ሲጠመቁ ስማቸውን ፍሥሐ ጽዮን ብለው ሰየሟቸው ይኸውም የቤ ተ ክርስቲያን ፍሥሐ መሆናቸውን በ መገንዘባቸው ነው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን እግዚአብሔር ተክለ ሃይማኖት ተ ብለው እንዲጠሩ ነገራቸው እንግዲህ ወዲህ ስምህ ፍሥሐ ጽዮን ሳይሆን ተክ ለ ሃይማኖት መባል አለበት አላቸው ። እንግዲህ ደግ ልጅ ለመውለድ እግዚአ ብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ መፈጸም ሕጉ ንም አለመተላለፍ ያስፈልጋል እግዚአ ብሔር በሕጉ ለሚመሩና በእውነት ለ ሚያመልኩት የለመኑትን አይነሣቸው ምና ፍሬው ደግ እንዲሆን ግንዱ መል ካም መሆን አለበት ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# በገና ጨዋታ...

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ሁሉ ጌታና መድኃኒት ስለሆነ በሱ ልደት ቀን ከበዓሉ ታላቅነት የተነሳ ትንሹም ትልቁም በአንድ ጨዋታ ላይ ተሰልፎ በሚጫወትበት ጊዜ ትልቁም ክብሬ - ተነካ መብቴ ተደፈረ አለማለቱ፣ ትንሹ ም አለመፍራቱ የሰዎች እኩልነት በክ ርስቶስ ዘንድ የተረጋገጠ ለመሆኑ አስ ተማማኝ ምስክር ነው ።

ዛሬም ቢሆን በሀገራችን በብዙ ቦታ ዎች የገና ጨዋታ የተቋረጠ ሳይሆን በ ተለይ በባላገር እየቀጠለ ያለ በመሆኑ በ ሁሉም ዘንድ የሚታወቅ ጨዋታ ነው

ይልቁንም ዓለም አቀፍ ይዘት ኖሮት ከ ሌሎች እስፖርቶች አንዱ ሆን እየተሠ ራበት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## የቄስ ሚስት አልሆንም

ወደ ትዳር ዓለም የሚያመሩ ወጣቶች ወንድም ሆነ ሴቷ በትዳር ዓለም ከመጠመዳቸው በፊት የኑሮ ጓደኛቸውን ይመርጣሉ በዚህ ጊዜ ከዚች ጋር እድሜ ልኬን መኖር እችላለሁ ብሎ ወንዱ ይወስናል ሴቷም እንደዚሁ ፤ በመጨረሻም ይጋባሉ እርግጥ የሰዎቹ መወሰን ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል የእግዚአብሔርም ፈቃድ ያስፈልጋል ። የእርሱ ፈቃድ ካልሆነ ሰው መቶ ጊዜ ቢያጠናና ቢወስን ላይሳካለት ይችላል ። ነገር ግን እንደ ፈቃድህ ይሁን የሚለውን ጸሎት እያስቀደሙ የሚያዋጣቸውን ማድረግና ማጥናት አስፈላጊ ነው ።

ይህንንም መነሻ በማድረግ ከአንዳንድ ወጣቶች ልጃገረዶች ጋር ስንነጋገር ለመሆኑ ቄስ ሊጋብቻ ቢጠይቃችሁ ፈቃደኞች ትሆናላችሁን ? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ከመካከላቸው አንዷ ወይዘሪት በቁጣ ቃል እኔ «የቄስ ሚስት አልሆንም» የሚል መልስ ሰጠች እኛም በመገረም ለምን ? አልናት መልሱም በዝርዝር እነሆ ።

ልሆን ከማልፈልግባቸው ምክንያት ጥቂቶቹን ልጥቀስ ስትል ወይዘሪትዋ ትጀምራለች የቄሱ ደመወዝ በወር ከ30 ብር ያልበለጠ ነው ከዚህም የተነሣ በቤት ውስጥ ኑሮው በጣም ዝቅተኛ ነው ።

ስለዚህ የቄስ ሚስት ብሆን ችግሩን እንዴት እቋቋመዋለሁ ? ልጅስ ቢወለድ እንዴት ያድጋል ? በኑሮየም ሁሉ ልደሰት አልችልም ከላይ እንደገለጽኩት በቂ ደመወዝ የለውም በቂ ደምወዝ ከሌለው ደግሞ እንደጓደኞቼ ልለብስና ላጌጥ አልችልም ይህም ቀርቶ በቤቱ ውስጥ በደንብ ምግብ ሠርቼ ለልጆቼም ም ሆነ ለኔና ለእርሱ ላቀርብ በፍጹም አልችልም ምክንያቱም በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል ካልበላን ካልጠጣን ካልለበስን ደስታ ፣ ፍቅር ፣ ሰላም ፣ ከየት ይመጣል እንጀትን አኮማትሮ ልብስን በደንብ ሳይለብሱ ፍቅር እኔ አላውቅም

ትልና ወ ት ግን እኮ ካህናት ቄሶች በቂ ደመወዝ የማያገኙበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ ? በማለት ተመልሳ እኛን ትጠይቀናለች ። እኛም ለምን ይመስልሻል ስንላት ለእኔ እንደሚመስለኝ በማለት ንግግሯን ትቀጥላለች ፤ በአንዷት ቤተ ክርስቲያን ከመቶ ያላነሱ ካህናት ይገኛሉ የቤተ ክርስቲያናዋ ገቢ ደግሞ ከ4እና ከ5 ሺህ

የማትበልጥ ምጽዋት ናት ያችም በወር ለዚያ ሁሉ ካህን ስትከፋፈል ታንሳለች ብየ እገምታለሁ ያም ሆኖ በወቅቱ የሚገኝ አይመስለኝም ምክንያቱም የሰበካው ምእመናን የወር መዋጮአቸውን በወቅቱ ከከፈሉ ያው ይገኛል ካልከፈሉ ግን እነርሱ ተለምነው እስኪከፍሉ ይዘገያል ካልሆነም ወደሚቀጥለው ወር ይሄዳል ። በውጭ ዓለም ግን በአንዷት ቤተ ክርስቲያን የተወሰኑ ቀሳውስት (አገልጋዮች) ይኖሯታል እንደኛው አይ

ንዛዛም እነሱም ከሌላው ሰው ያላነሰ ኑሮ ይኖራሉ ልጆቻቸውንም በደንብ ያሳድጋሉ ፤ ካህን ማግባትም ከጥሩ ኑሮ ጋር ያስደስታል ። ሌላው ምክንያቴ ደግሞ ትላለች ወ ት ቄሱ አንድ ዓይነት አደጋ ቢደርስበት እንኳን ማለት በሞት ከዚህ ዓለም ቢለይ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ መ ቤቶች በቂ ጡረታ ለቤተሰቡ አትከፍልም ቄሱ በሕይወቱ እያለ ሌሊት በሰዓታት ቀን በአገልግሎት በማስተማርና በመሳሰሉት የሥራ ዘርፎች በትንሽ ጉርሻ እድሜ ልኩን ሲያገለግል ኖሮ የሞት ሞት ሲሞት ደግሞ ለልጆቹ ማሳደጊያ ጡረታ አያገኝም ታዲያ የእርሱን ልጆች ምን እያበላሁና እያጠጣሁ አሳድጋቸዋለሁ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች የካህናት ሚስቶች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የሚረዱበት አነስኛ ሥራ አትሰጥ ከዚያ ገብቶ ችግሬን አቃልላለሁ እንዳልል ኧረ እባካችሁን ብዙ አታናግሩኝ የስንቶቹ ካህናት ልጆች ናቸው ድሃ አደግ ሆነው የቀሩት ምክንያቱም አባቶቻቸው ከሞቱ በኋላ መተዳደሪያ ስለሌላቸውና እናትየዋ በደንብ አስተምራ ልታሳድጋቸው ስለማትችል ነው ። ዛሬ እርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንዶች ክፍላተ ሀገር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስም የተቋቋሙ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች አሉ በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥም ብዙዎቹ የካህናት ልጆች ይገኛሉ ሲባል ሰምቻለሁ ታዲያ በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ብዙዎች የካህናት ልጆች ሊኖሩ የቻሉበት ምክንያቱ ምንድነው ? ምክንያቱ ግልጽ ነው ቄሱ ከሞተ በኋላ ሚስቱ ማሳደግ ስለማትችል በሕይወት ቢኖርም በቂ መተዳደሪያ ስለሌለው ነው ። ይሁን እንጂ ድርጅቱስ ስንቱን ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ ።

ብቻ ወሬ አበዛሁኝ እንጂ በሌላው ዓለም እንደምንሰማው የካህን ( ቄስ ) ሚስት የምትሆን የታደለች ናት ይባላል አሉ ምክንያቱም የካህን ሚስት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ የሥራ ተሳትፎ አላት ካህኑ ባሏ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግለውን ያህል እርሷም ትሠራለች በካህኑ መጠን በተለያየ የሥራ ዘርፍ ህብረተሰቡን ታገለግላለች ስለዚህም የካህን ( የቄስ ) ሚስት መሆን እጅግ አስደሳች ነው እውነተኞች ካህናት አይሰክሩም አያመነዝሩም ደስታቸው ሁሉ በቤታቸው ውስጥ ነው ስለዚህ ሚስቶቻቸው ደስተኞች ናቸው ።

በሃገራችን ግን እንደዚህ አይደሉም ያው እንደምታውቁት እንኳንስ የካህኑን ያህል ልትሠራ ይቅርና የቄሱ ሚስት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀዋሚ የሆነ የሥራ ዘርፍ የላትም ግን ይቅርታ አድርጉልኝና በቤተ ክህነት ውስጥ የተቀጠሩ ካሉ አላውቅም ቢኖሩም ብዙሃኑን ሊወክሉ አይችሉም ።

ስንቱን አውርቼ እዘልቀዋለሁ እንጂ ሌላው ደግሞ እንደምመለከተው ከሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የሚኖራቸው ሚስት ያላገቡ ( መነኮሳት ) ናቸው ። ስለዚህ ሚስት ያገቡ ቀሳውስት ከፍተኛ ስልጣን እንደማይገባቸው ስለሚታዩ የእነርሱ ሚስቶች ክብር አይሰጣቸውም ። ይህም በዓይናችሁ የምታዩት ነው ሌላም ማስረጃ እንዲሆናችሁ አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ ግን እንዳታዝኑ አንድ ስመ ጥር ግሪካዊ ካህን ( ቄስ ) ነበሩ ካህኑ እጅግ ተናጋሪና አስተማሪ ባለድግሪ ነበሩ ታዲያ ከፍተኛ ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚመኙ የግሪክ መነኮሳት የእኚያ ካህን ሚስት እንድትሞት ይመኙ ነበር ። ነገር ግን የእግዚአብሔርና የሰው ሀሳብ የተለያየ ስለሆነ እኚያ ካህን ከሚስታቸው በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። በዚህ አንጻር እኔም ቄስ ባገባ የማገባው ካህን ከፍተኛ ደረጃ እንዳያገኝ ጠንቅ እሆንበታለሁ ወዳጆቹና ዘመዶቹም እርሱ ከፍተኛ ሥልጣን እንዲያገኝላቸው የኔን መሞት ይመኙ ይሆናል ማለት ነው ከዚህ ሁሉ ቢቀርብኝስ ።

ሌላው ችግሬ ቀሳውስት ብዙ ጊዜ በህብረተሰቡ መካከል ለሥራ ትጉሆች እንዳይደሉ ይነገራል ። ስለዚህም «ልጁን የጠላ ለደብተራ ከብቱን የጠላ ለአደራ» ይሠጣል ። እየተባለ ይተረትባቸዋል ። ይህም አንዱ እንቅፋት ነው ። ምን ያህል እውነት እንደሆነ ግን አላውቅም እንግዲህ በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ሌሎች ምክንያቶች የቄስ ሚስት አልሆንም ስትል ወይዘሪትዋ አስተያየትዋን አበቃች ።

አዎ ማንም ሰው ምርጫውን መወሰን መናገርም መብቱ ነው ። ወይዘሪትዋም ቄስ ለማግባት የማትፈልግበትን ምክንያቶች ግልጽ በሆነ አማርኛ የመሰላትን የሚሰማትን ተናግራለች ግን ወይዘሪትዋ የተናገረቻቸው የኑሮ እንቅፋቶች የሚወገድ ከሆነ የቀሳውስት ሚስቶች እድለኞች መሆናቸውን በገለጠችበት አንቀጽ እርስዋ የቄስ ሚስት ለመሆን ፈቃደኛ ነበረች ይሁን እንጂ ችግሮች እስካሉ ድረስ የቄስ ሚስት ለመሆን ፈቃደኛ አልሆንም ትላለች ።



## የግእዝ ትምህርት በመንፈሳውያን ት ቤቶች

ግእዝ በአሁን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ት ቤቶች ለምሳሌ በምሳካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለምና በካቶሊክ ቤ ክ ት ቤቶች ወዘተ .. በዘመናዊ አቀራረብ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል ።

ከጥቂት ዓመታት በፊትም በመንበረ ፀባዖት ቅ ሥላሴ ካቴድራል « ሥላሴ ትምህርት ቤት » በዘመናዊ አቀራረብ በተሟላ ሁኔታ የግእዝ ትምህርት ይሰጥ ነበር ። ይሁን እንጂ የግእዙና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለምን እንደተቋረጠ የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ ዲያቆን ክፍ ያለው መራሂ ተጠይቀው የሚከተለውን መስል ሰጥተዋል ።

ቀደም ሲል በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊና ዘመናዊ ት ቤት የግዕዝ ቋንቋ ይሰጥ ነበር ፣ አሁን ለምን ተቋረጠ ? ወደፊትስ እንደገና የሚቀጥልበት ጥናት አለ ወይ ?



የቅ , ሥላሴ ዋና ጸሐፊ ዲ/ ክፍያለው መራሂ

ዲያቆን ክፍያለው ፥ - በውነቱ ይህ ጥያቄ መሠረታዊና አስፈላጊ ጥያቄ ነው በመሠረቱ « ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ » እንደተባለው ይህ ትምህርት ቤት ሲጀመር በካቴድራሉ ውስጥ ለሚያገለግሉ መነኮሳትና ዲያቆናት በጠቅላላውም ለካህናት ማሠልጠኛ ነበር ። ይህ ም ይታወቅ ዘንድ የግእዝ ቋንቋና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓመት እስከ ዓመት በሚገባ ከተሰጡ በኋላ በዓመቱ መጨረሻ ላይ እንደማገኘውም የትምህርት ዓይነት የፈተናው ውጤት በካርድ ላይ ይሞላ ነበር ። እንደ እንግሊዝኛ ፣ ሳይንስና የስሌት ትምህርት ዋጋ ነበረው ።

ቀስ በቀስ ት ቤቱ ዝነኛ እየሆነ ሲሄድ የካህናት ት ቤት ብቻ መሆኑ ቀርቶ የአካባቢው ልጆች ወደዚህ ት ቤት መግባት ጀመሩ ፣ ጥቅሙን እየተረዱት ሲሄዱ እንደማገኘውም የትምህርት ዓይነት በግእዝ ቋንቋና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከፍተኛ ፍቅር አደረባቸው ። የዚህ ትምህርት ቤት ነገር ሲነሣ ሁልጊዜ ከማስታውሳቸው ነገሮች አንዱ እኔ እራሴ ሰባተኛ ክፍል በነበርኩበት ወቅት



www.ethiopianorthodox.org

ከአራት ኪሎ አካባቢ ከሚመጡት ተማ
ሪዎች መካከል አንድ ሁሴን የሚባል
የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ተማሪ
ነበር ፣ የግእዙንና የመጽሐፍ ቅዱሱን
ጥናት ከእኛው ጋር ዓመቷን በሙሉ ሲከ
ታተል ከርሞ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በ
ፈተና አንደኛ ወጥቶ ከመካከላችን የ
መጽሐፍ ቅዱስና የግእዝ መጽሐፍ ተ
ሸልሟል ።

ከዚህ ላይ ለእኔ እንደ ተረዳኝ ፍሬ ነ
ገሩ ልጁ ተማሪ ሁሴን ከሃይማኖት
አንፃር ሳይሆን በግእዙ ቋንቋና በመጽ
ሐፍ ቅዱሱ ፍልስፍና ጥልቀትና ምጥቀ
ት ነው ልቦናው የተነካ ።

«ሠምና ወርቅ » የሚለውንም ዘይቤ
ልጆቹ በበለጠ ሊረዱት የሚችሉት የግ
እዝን ቋንቋ ሲያጠኑ መሆኑ ግልጽ ነው።
አንአንድ ሊቃውንት እንደሚተነትኑት
ሠምና ወርቅ የሚለው አነጋገር በኢት
ዮጵያውያን የቅኔ መንገድ ብቻ ሳይሆን
በጠቅላላው የኅብረተ ሰቡን የኑሮ ጠባ
ይ የሚገልጽ ፍልስፍና ነው ይላሉ ።

በእርግጥ ለጥቂት ዓመታት በዚህ ት
ቤት እነዚህ የትምህርት ዓይነቶች በሥ
ርዓተ ትምህርታችን ላይ መቋረጣቸውን
አንክድም አሁን ግን እንደገና ለመጀመ
ር በጥናት ላይ እንገኛለን ።

እራሱ የት ቤቱ ስም ቅድስት ሥላሴ
መንፈሳዊና ዘመናዊ ት ቤት ስለሚል
ስሙና ግብሩ ጥርስና ከናፍር ሆነው አ
ብረው እንዲሄዱ ይታመንበታል ። እን
ደ እኔ አስተሳሰብ እንኳንስ በቤተ ክርስ
ቲያን ጥላ ስር በሚካሄዱት ት ቤቶችና
ከተቻለ በሙላ ኢትዮጵያም ት ቤቶች
የግእዝ ቋንቋ ቢሰጥ ከመሠረተ ትምህ
ርት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች
ወደፊት የምርምር ጥናት በእራሳችን
ቋንቋ እንዲሆን የቋንቋው አካዳሚክ ለ
ሚያደርገው ከፍተኛ ጥረትና ምኞት ሰ
ፊ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል ብዬ
ሙሉ በሙሉ አምንበታለሁ ።

በአንድ በኩል የግእዙ ቋንቋ ቅኔንና
ፍልስፍናን አጣምሮ ስለሚይዝ የልጆ
ቹን የአስተሳሰብ አድማስ ሊያሰፋው ይ
ችላል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው
የአማርኛ ቃላት ከግእዝ ቋንቋ ጋር ስለ
ሚወራረስ ተማሪዎቹ ከየት መጣውን
በቀላሉ ሊረዱትና ሊያውቁት ስለሚች
ሉ ቋንቋውን እንደፈለጉ ሊያዙት ይችላ
ሉ ። ለምሳሌ በአያሌ የአውሮፓ አገሮ
ች በመሠረተ ትምህርት (በኢለመንታ
ሪ) ት ቤቶች ሕፃናቱ በላቲን ቋንቋ አ
ፋቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል ። ምክንያ
ቱም ለአብዛኛዎቹ የአውሮፓ ቋንቋዎ
ች መሠረታቸው ላቲን በመሆኑ ልጆቹ
ከፍተኛ ሳይንሳዊ ጥናት ሲያካሂዱ ብዙ
ሳይንትፊክ የሆኑ ነገሮች የላቲን ስም
ስለተሰጣቸው ችግር እንዳይገጥማቸው
መሆኑ ግልጽ ነው ።

ከዚህ ላይ ኢትዮጵያዊው ሊቅ የአለቃ
ኪዳነ ወልድ ክፍሌን ግጥም ለመጥቀስ
እወዳለሁ « ላቲን ለአውሮፓ እንዲያስ
ፈልገው ለኢትዮጵያም ግእዝ ግድ ነው»
ሀሳቡ ግልጽ ይመስለኛል የአባቶቻች
ንም የአነጋገር ዘይቤ እንዲህ ይላል «ለ
አማርኛ ግእዝ ነው ዳኛ » ። ለምሳሌ በ
አንድ ቃል ሀሳቡን አጠቃሎ ለመናገር
ወይም ጽሑፋችን ውበትና ለዛ እንዲኖ
ረው ስንፈልግ ከግእዝ የምንወስዳቸው
ቃላት ቅመም ሁነው ዐረፍተ ነገርን ያ
ጣፍጡልናል ። ለምሳሌ ሕገ መንግሥ
ት ፣ ሥርዓተ - ትምህርት ፣ ሥነ - ምግ
ባር ፣ ክብረ - ህሊና ፣ ርእዮተ - ዓለም -
ወዘተ የመሳሰሉትን ቃላት ብንመለከት
ምን ያህል የግእዝ ቋንቋ አስፈላጊ መሆ
ኑን ለመገንዘብ አያዳግትም ።

ለምሳሌ የበሬ ግንባር የሚያካክሉ ጥ
ቃቅን የአውሮፓ አገሮች ከፍተኛው የ
ምርምር ጥናት በራሳቸው ቋንቋ በመሆ
ኑ ልጆቹ ከፍልስፍናው ጋር ነው እንጅ
የሚታገሉ ከቋንቋው ጋር አለመሆኑ ግል
ጽ ነው።ነገር ግን በሀገራችን ያለው ችግ
ር አብዛኛውን ጊዜ ከታች እስከ ላይ ድ
ረስ ልጆቹን ያስጨንቃቸዋል ፣ አንድም
ሀሳባቸውን እንደፈለጉ እንደመስኖ ው
ኃ ለማዘዝ አይችሉም ። ምክንያቱም ቋ
ንቋ የሀሳብ መግለጫ መሣሪያ እንደመ
ሆኑ መጠን ተማሪዎች በባዕዳን ቋንቋ
ያላቸው መሠረት እንኳንስ ፍልስፍናን
ለመተንተን ለመራቀቅ የሰላምታ ደብ
ዳቤ ለመጻፍም የማያዝናናቸው መሆኑ
የአደባባይ ምሥጢር ነው ።

ስለዚህ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ
ና ዘመናዊ ት ቤት የግእዝን ቋንቋና
መጽሐፍ ቅዱስን ከአንደኛ ክፍል
ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ዘመናዊ በሆነ
የአቀራረብ ዘዴ ለመስጠት በጥናት
ላይ እንገኛለን ። ምንጊዜም ቢሆን ኦርቶ
ዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናች
ን ቋንቋን ፣ ሃይማኖትን፣ ሥነ ምግባርን
ጠቃሚ ባህልን ፣ የሀገር ፍቅርን ሙዚ
ቃን በጠቅላላው ሥነ - ጥበብን ከትውል
ድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ታሪካዊ
ግዴታዋ መሆኑን አትዘነጋውም ።

## ይህን ያውቁ ኖሯል ?

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ያገኘ ከደከሙ ሰዎች አንዱ ነው ያሉለ
ት ሰው ነው ። የወንጌል መልእክተኞ
ቹ እሱን ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለመመ
ለስ በሚጣጣሩበት ጊዜ ፣ « እናንተ ሃይ
ማኖታችሁን እንደፈለጋችሁ አድርጉት
ብቻ ክርስቶስን እንዳትነኩብኝ » ይል
ነበር ።

ጋንዲ እስከዚህ ድረስ ልቡ በክርስቶስ
ፍቅርና ትምህርት የተቃጠለ ሰው ነበ
ር ። ስለ ክርስስቶስና ስለ ትምህርቱ የገ
ለጠው ፍቅርና የሰጠው ምስክርነት ክ
ርስቶስ ታላቅ መምህር መሆኑን ያረ
ጋግጣል ። እውነተኞች ክርስቲያኖች
ግን ክርስቶስን « ታላቅ መምህር » ነበ
ር በማለት ብቻ አይወሰኑም ። እርሱን
በማክበርና ትምህርቱን በማድነቅም
ብቻ የሚቀሩ አይደሉም ። እርሱ ስለ ሰ
ው ልጆች ድኅንነት በሥጋ የተገለጠ እ
ውነተኛ አምላክና መድኃኒት መሆኑን
ያምናሉ ። የትምህርቱም ብርሃን በሕይ
ወታቸው እንዲገለጥ ያደርጋሉ፡በመልካ
ሙ ሥራቸው የሰማዩ አባታቸው እንዲ
መሰገን ይፈልጋሉ ።

እጅጉ ረታ



# የጾመ ነቢያት ስሙና ብያኔው

1ኛ ስሙ ጾመ ስብከት ይባላል ይኸ
ውም ይወርዳል ይወለዳል አዳምን ወደ
ቀደመ ቦታው ሊመልስ ይመጣል እየተ
ባለ የተነገረውን ትንቢት የተቆጠረው
ን ሱባዔ ከአበው ሲወርድ ሲዋረድ የመ
ጣውን ስለሰበኩ ስለአስተማሩና በዚሁ
ምክንያት አርባ አርባ ቀን ስለጾሙ ስ
ሙ ጾመ ስብከት ተብሏል ።

2ኛ/ ጿሚዎች ነቢያት ስለሆኑ በጿ
ሚዎቹ ስም ጾመ ነቢያት ተብሏል ።

3ኛ/ ጾሙ የሚፈጸምበት ማለት የሚ
ፈሰክበት የገናዕለት የልደት ዕለት ስለ
ሆነ ጾመ ስብከተ ገና ወይም ጾመ ልደት
ተብሏል ።

4ኛ/ ጾመ ማርያም ተብሏል ይኸንኑ
ሲያትቱ ጌታን ከመውለዱ አስቀድሞ
የጾመችው መሆኑን በፍትሐ ነገሥት
ትርጓሜ ላይ ያትታሉ ፤ ይሁን እንጂ ከ
ላይ በተጠቀሰው ማለት ጾመ ነቢያት
በሚለው መሠረት በመጀመሪያ እንደ
ሙሴ እንደ ኤልያስ እንደ እዝራ ያሉ
አበይት የጾሙት መሆኑ የማይካድ ነው
እነዚህም የጾሙት ለአንድ ጊዜ ብቻ መ
ስሎ ይታያል ። ይሁን እንጂ ወደ አቡ
ሻክር መጽሐፍ መለስ ብለን የተመለከ
ትን እንደሆነ ከዘጠኙ የብሉይ አፅዋ
ማት አንዱ ጾመ አይሁድ ወይም ጾመ
ሙሴ ተብሎ ከመጸለት ቀጥሎ 4ኛ ተራ
ቁጥር ይዞ ይገኛል ።

ስለዚህ በዘመነ ብሉይም ቢሆን ለአ
ንድ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየዓመቱ
እንዲጾም በሕግ መሰራቱን ያስረዳናል፡

አሁን ከዚህ ላይ ለአንባብያን ስለ
ጾመ ነቢያት ታሪክና ብያኔ ለመጻፍ የተ
ነሳሁበት ዋና ምክንያት በየዓመቱ የጾ
ሙ የመጀመሪያ ቀን ኅዳር 15 ወይም
መንፈቀ ኅዳር 16 ነው በማለትና እንዲ
ሁም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሶስ
ቱን ቀናት ችላ በማለት ጾማቸውን ኅዳ
ር 19 ቀን የሚጀምሩ ወገኖች ስለአሉ
ሁሉንም በተራ ቁጥር በመዘርዘር ምክ
ንያቱን በተቻለ መጠን ለመግለጽ ያህ
ል ነው ።

1ኛ ኅዳር 19 ቀን ጀምረው ታህሣሥ
29 ቀን የሚፈጽሙ ሌሎች አብያተ ክ
ርስቲያናት ይገኛሉ የተባሉት ወገኖች
ስንክሳር ከመጻፉ ማለት ከአረብኛ ወደ
ግዕዝ ቋንቋ ከመመለሱ አስቀድሞ ሲሰ
ራበት የነበረውን አዋጅ የሚከተሉ ናቸ
ው ይኸም ሲቆጠር ልክ 40 ቀን ብቻ
ይሆናል ይኸውም ወበዛቲ ዕለት ጥንተ
ጾመ ስብከተ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ሎቱ ስብሀት ዘሰርኡ ለክርስ
ቲያን ያዕቆባውያን ባለው ይታወቃ
ል ስንክሳር ኅዳር 19 ቀን ተመልከት
2ኛ ስንክሳር ከአረብኛ ወደ ግዕዝ ቋን
ቋ በተመለሰበት ዘመን አካባቢ የኢትዮ
ጵያ ሊቃውንት በጾመ ስብከት ውስጥ
የአብሳሪ ፣ የተበሳሪ ፣የመበስር በዓል 3
ቀን በጥሉላት እንዲከበር ተደርጓል
ይኸውም ሀ ታህሣሥ 19 ቀን ያብሳሪ
በዓል ተብሎ በጥሉላት እንዲከበርለ ታ
ህሣሥ 3 ቀን የተበሳሪ በዓል ተብሎ በ
ጥሉላት እንዲከበር

ሐ ታህሣሥ 22 ቀን የመበስር በዓል
ተብሎ በጥሉላት እንዲከበር ነበር ።ነገ
ር ግን የመበስር በዓል በታህሣሥ ወር
ሊሆን የቻለበት ምክንያት በጾመ አርባ
መካከል መጋቢት 29 ቀን በዓሉን በጥ
ሉላት ማክበር ስለማይቻል ነው ። በዓ
ሉን ለማክበር ሊቃውንቱ በዚህ ውሳኔ
ከተስማሙ በኋላ በእነዚህ በ3ቱ ቀና
ት ምትክ ሶስት ቀን ለመጾም ጾመ ስብ
ከትን ከኅዳር 19 ቀን ወደ ኅዳር 15 ቀን
አወረዱት ይኸውም ወውእቱ ጾም ዘይ
ቀድም እምልደት ወጥንተ ዚአሁ መን
ፈቀ ኅዳር ወፋሲካሁ ልደት በአለው ይ
ታወቃል ፍት ነገ አንቀጽ 15 ተመልከ
ት ይኸም ሲቆጠር ልክ 43 ቀን ይሆናል
ይኸውም 40ው ቀን ጾመ ነቢያት ሲሆን
ሶስቱ ቀን በአብሳሪ በተበሳሪና በመበ
ስር በዓል ምትክ የገቡ ናቸው ከአቡሻ
ከር መምህሬ ያገኘሁት የእጅ ጽሑፍ ታ
ሪክ ገጽ 8

በዚህ ጊዜ ጾመ ገሃድስ ወዴት ቀረ የ
ሚል ጥያቄ እንደሚቀርብ አያጠራጥር
ም ይሁን እንጂ ጾመ ገሃድ እስከዚህ ዘ
መን ድረስ በዓመት በዓመቱ እንዲጾም
አልተወሰነም ነበር ምክንያቱም ጾምነ
ቱ የሮብና የዐርብ ለውጥ ነበርና ። ይኸ
ውም ልደት ረቡና ዐርብ በሚውልበት
ዘመን ረቡ ወይም ዐርብን በጥሉላት
ለማክበር ወይም ዓርብን በጥሉላት ለማ
ክበር ማክሰኞን ወይም ሐሙስን እስከ
ሰዓት መጾም የክርስቲያን ሁሉ ግዴታ
ነበር ይኸውም የረቡዕና የዓርብ ለውጥ
ለመሆኑ "ዘውእቱ ተውላጠ ረቡዕ
ወአርብ በማለቱ ይታወቃል (ፍት ነገ)

መጽሐፈ ስንክሳር ከዓረብኛ ወደ ግዕ
ዝ ቋንቋ ተስተካክሎ ከተመለሰ በኋላ የ
ተጻፈው ስንክሳር የኢትዮጵያ ሊቃውን
ት ጾመ ገሃድ የረቡዕና የዓርብ ለውጥ
መሆኑ ቀርቶ በየአመቱ የልደት ዋዜማ
ና የጥምቀት ዋዜማ በአዋጅ ሰኞም ማ
ክሰኞም ቅዳሜም እሑድም ቢውል ጾ
መ ገሃድ ተብሎ እንዲጾም ስለወሰኑ ከ
ኅዳር 15 ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ29
ቀን ድረስ ይጾማል ይኸውም "ወበዛቲ
ዕለት ካዕበ ጥንተ ጾመ ስብከተ ገና ልደ
ቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ
ስብሐት ዘሰርኡ ለክርስቲያን ያዕቆባው
ያን" ባለው ይታወቃል ። ይኸም ሲቆ
ጠር ልክ 44 ቀን ይሆናል ይኸውም 40
ው ቀን ጾመ ነቢያት ሶስቱ ቀን በአብሳሪ
በተበሳሪና በመበስር በዓል ፈንታ የገቡ
ቀናት ሲሆኑ አንዱ የገሃድ ጾም መሆኑ
ግልጥ ነው ነገር ግን ከጥቂት ዓመታት
በኋላ የተነሱ ሊውንት ይኸንን የአብሳ
ሪ የተበሳሪና የመበስር በዓል ተብሎ
በታህሣሥ ወር እንዲከበር የተወሰነው
ን ውሳኔ

ሀ በዋዜማ ሰራተኞች የሚሠሩትን ወ
ይም ሰርተው የሚያቀርቡትን የማይቀ
ምሱበት

ለ በማግስቱ ከበዓሉ የተረፈውን የማያ
ከናውኑበት በዓል በጥሉላት ሊከበር አ
ይገባውም በማለት በጥሉላት መከበሩ
ቀርቶ በስብሐተ እግዚአብሔር ብቻ እ
ንዲከበር ተዱርጓል ነገር ግን እነዚህ በብ
ሳሪ በተበሳሪና በመስበር በዓል ምትክ ሆ
ነው እንዲጾሙ የተወሰኑት ሶስቱ ቀናት

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ

## "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ"

በኢትዮጵያ በደማቅ ሁኔታ የሚከበሩ በርከት ያሉ መንፈሳዊያን በዓላት የመኖራቸውን ያህል እያንዳንዱ ዓመት በዓል የተለየ ምሥጢርና የታሪክ ፣ ገጽታ ስላለው ወጣቶች በየበዓላቱ የሚጫወቷቸው ጨዋታዎችም እንዲሁ የተለያየ ባህልና ይዘት አላቸው ።

ባለፈው ጊዜ "ወጣቶች ከቡሄ እስከ መስቀል" በሚለው ጽሑፍ እንደተጠቀሰው በዘመን መለወጫ ፣ በቡሄና በመስቀል በዓል ወጣቶች ምን ዓይነት ጨዋታ እንደሚጫወቱ ለመግለጥ ተሞክሮ እንደነበር የሚታወስ ነው ። በአሁኑ ዝግጅት ደግሞ የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በዚሁ ወቅት ወጣቶች ስለሚጫወቱት የገና ጨዋታ ቀጥሎ የተመለከተውን አቅርበናል ።

በመሠረቱ የገና በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ዕለት ነው። ታዲያ ይህን በዓል ምክንያት በማድረግ ወጣቶች ሁሉ ገና ጨዋታ በመጫወት በዓሉን በደስታ ሲያሳልፉት ኑረዋል ። ይህም በሁለት ቡድን ተከፍለው ሩር በመምታትና በመላጋት የሚያካሂዱት የጨዋታ ዓይነት ነው ። ስለዚህም የገና በዓል ከመድረሱ አስቀድሞ በታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ በዕድሜ በሰል ያሉት ወጣቶች እየተመራረጡ በየአካባቢያቸው ልምምድ ሲያደርጉ ይሰነብታሉ በሌላም በኩል በበዓሉ ዕለት የሚጫወቱበትን ጥንግ ሩር ከእስታ ጉቶና ከሌላም ከባድ ካልሆነና ቀለል ካሉ እንጨቶች ጠርበውና አለስልሰው እንደኳስም ድብልብል አድርገው ያዘጋጃሉ ቆዳውን በቀጭን ጠፍር ሰፍተው እንደኳስ አድበልብለው የሚያዘጋጁም አሉ ።

ወጣቶች በገና ጨዋታ የሚያዘጋጁት ሩር ብቻ አይደለም ሩሯን ለመምታት ለመለጋትና ለመቆራቆስ አመች የሚሆኑ ዱላዎችንም እንደዚሁ በነፍስ ወከፍ አዘጋጅተው ነው የገናን በዓል መድረስ ሲጠባበቁ የሚቆዩት ። ወላጆቻቸው ደግሞ ዳቦውን ጠላውን ፣ ለእርድ የሚሆኑ እንስሳትን እንደ ዓቅማቸውና እንደችሎታቸው ሲያዘጋጁ ይቆያሉ ። በነገራችን ላይ በሀገራችን በኢትዮጵያ "የገና ዳቦ" ዝና ያለው በመሆኑ "ዓመት ቢደክሙ እግዚአብሔር ካልባረከው ለገና ዳቦ አይበቃም" እየተባለ ይተረታል ፣ በሌላም በኩል "ዓመት ሠርቶ ለልደት------እየተባለም ይነገራል ይህ ሁሉ የገናን በዓል ታላቅነትና ክቡርነት የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ የቤት መሰናዶው ዝግጅትም ከሌሎቹ በዓላት ላቅ ያለ መሆኑን የሚጠቁም ነው ።

የገና በዓል ዕለት እስከ ሰዓት ድረስ በብዙ ድካም የቀረበውን መሰናዶ በመብላትና በመጠጣት ሲደሰቱ ከቆዩ በኋላ የጨዋታው ጊዜ ሲደርስ ወጣትነት ያላቸው ሁሉ በእድሜ ከፍ ያሉት ገበሬዎች ሳይቀሩ የገና መምቻ ዱላቸውን እየያዙ እንዳንዶችም መርኮዝ እያሉ ወደ ተለመደው የገና መምቻ ሜዳ ያመራሉ

አዛውንቶች ለዚህ ጨዋታ ዓቅማቸው የማይፈቅድላቸው ወጣቶችና ሕፃናትም ጭምር ወደሜዳው ሄደው በሜዳው ዳርና ዳር እየቆሙ ጨዋታውን ለመመልከት ይዘጋጃሉ ። ሕዝቡ በብዛት እንደተሰበሰበ እንጫወታለን ብለው በራሳቸው የሚተማመኑና ዕድሜያቸውም የሚፈቅድላቸው ወደመካከል ሜዳ ይገቡና የጨዋታውን ሕግ ከሚያውቁት በግጥም መስደብ ከሚችሉት በጨዋታቸው ተደማጭነት ካላቸው መካከል ሁለት ሰዎች "የቡድን አባቶች" ተብለው እንዲመረጡ ይደረጋሉ ። የቡድን አባቶች ሆነው የተመረጡት ደግሞ በበኩላቸው ተጨዋቾችን መርጠው ለየቡድናቸው ያሳልፋሉ ። ይህም ሲባል የአመራረጥ ሕግ እንደሀገሩ ልማድ ሊለያይ ይችላል ።

ለምሳሌ በአንዳንድ ቦታ ቆላና ደጋ ለይተው የሚጫወቱ ሲኖሩ በአንዳንድ ቦታ ደግሞ ወገን ለይተው ሁሉም በየመልከኛቸውና በየአጥቢያቸው ተመራርጠው በቡድን የሚሰለፉ አሉ ። በዚህ ጊዜ የቡድን መሪዎች የሚመርጡት እንደተጨዋቾቹ ከየወገኑ ይሆናሉ ። በአንዳንድ አካባቢ ግን ወገን ሳይለይ ከሁሉም የተወጣጡ ሁለት የቡድን አባቶች በጠቅላላው ተጨዋቾች ተመርጠው ከተሰየሙ በኋላ እነሱ ደግሞ ተጨዋቾች



በሚመርጡበት ጊዜ ለምርጫ የሚቀርቡት ተጫዋቾች ሁለት ሁለት እየሆኑ ለየራሳቸው መጠሪያ ስም በመስጠት አንደኛው ነብር ሌላው አንበሳ ፣ እንዲሁም አንዱ ስንዴ ሲሆን ሌላው ደግሞ ገብስ ወዘተ እየተባባሉ ወደቡድኑ መሪዎች እየቀረቡ ከነብር ከአንበሳ ፣ ከስንዴ ከገብስ ብለው በመናገር የቡድን አባቶች እንዲመርጧቸው ይደረጋግና የቡድን መሪዎች ከነብር ከአንበሳ ወይም ከስንዴ ከገብስ አማርጠው ለራሳቸው የወደዱትን ይጠራሉ ። ይህም ሲባል "ነብር ፣ አንበሳ ገብስና ስንዴ--" ተብሎ የተሰየመው ማንኛው ተጨዋች እንደሆነ ስለማያውቁ ከእገሌ እገሌ ይሻላል ብለው ሰወቹን ለማማረጥ ዕድል አያገኙም ። ምክንያቱም ገብስ ወይም ነብር ወደኔ ና ሲሉት እኔነኝ ብሎ የመጣውን መቀበል እንደሚኖርባቸው የገና ጨዋታው ሕግ ስለሆነ ነው ።

በዚያም ሆነ በዚህ የምርጫው ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ በሜዳው ተቃራኒ ቦታዎች ዕጣ ተጣጥለው የግብን ክልል ወስነው ጨዋታው በመካከል ሜዳ ላይ ይጀመር ዘንድ ከሁለቱ ቡድኖች የተመረጡ ተጫዋቾች የገና መምቻ ዱላቸውን ይዘው መቆራቆስ ሲጀምሩ በመካከል ሩር ትጣልና በዚህ ጨዋታው ይጀመራል ወዲያውም የበረታው ክፍል ወደ ግቡ ይመታታል ከዚያ በኋላ ሁሉም ለተሰለፉበት ቡድን በመጫወት የተቻለውን ያህል እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ። ከብዙ ትግል በኋላ ከሁለቱ አንደኛው ቡድን አይሎ ግብ ሊያገባ ይችላል ።

በአሁኑ ጊዜ የምናየው የሱስ ጨዋታ የራሱ የሆነ ሕግ እንዳለው ሁሉ ለገና ጨዋታም የተለያዩ ሕጎች ስለአሉት አጫዋቾቹ ጨዋታውን የሚመሩትም በዚሁ ሁኔታ ነው ። በገና ጨዋታ ሕግ መሠረት ሩሯን ከአየር ላይ ካልቀለበ ወይም ሩሯ መትታው ጉዳት ካላደረሰችበት ማለት በሰውነቱ ላይ ካላረፈች በቀር ከመሬት አንሥቶ መለጋት የማይችልበት ቦታ አለ ። በዚህ ጨዋታ በአየር ላይ እንዳለች ሩሯን ቀልቦ ወደ ግቡ የሚለጋ ወይም ሳይቀልብ በዚያው በአየር እንዳለች በብትሩ ለግቶ ወደ ግቡ የሚመልስ ተጫዋች የበለጠ ይደነቃል ።

በጨዋታው ጊዜ ተጠንቅቀውና ረጋ ብለው የማይጫወቱ ሰዎች ብዙውን ጊዜ አደጋ ሲያጋጥማቸው ይችላል ። ከዚህም የተነሣ ዓይናቸው እየፈሰሰ ጥርሳቸው እየወለቀና እግራቸው እየተሰበረ ከጨዋታ የሚገለሉ ነበሩ ።

በዚህ ጨዋታ የበለጠ ለማጥቃት ዕድል ያለው የመመረጥ ኃይልና ሩሯን ለመምታት ፍጥነት ቅልጥፍናና ዘዴ ያላቸው ተጨዋቾች ያሉበት ቡድን ነው በዚያም ሆነ በዚህ በርትቶ ግብ ያገባው ቡድን አሸናፊነቱን ካረጋገጠ በኋላ ተሸናፊውን ወገን ስም እየጠራ የሚችለውን ያህል በግጥም ይሰድበዋል። ለምሳሌ ከግጥሞቹ ጥቂቶቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

ሆዬ በል ሆዬ ፡-
እየው አካሄዱን አረማመዱን ፣
እንደቃሪያ ሎሚ ወጥሮ ሆዱን ።
ጌታው አቶ እገሌ ትላንትና ማታ የበላው ሽልጦ
አላስሮጠው አለ እጎኑ ተሸጦ
አሆዬ ፡- የኔማ አቶ እገሌ ልንገርህ አንቅሬ
የብሳና ዱላ አፍህ ውስጥ ቀርቅሬ
አሆዬ ፡- ጥንግ ናት ሩር የምትሽከረከር፣
የኔማ አቶ እገሌ ምን ትፈራታለህ እንደ አራስ ነብር ፣
ረጅሙን ሲሰድቡ ፡-
ይኸን ረጅሙን ጎማምዶ ጎማምዶ ፣
ግማሹን ለአርጩሜ ግማሹን ማገዶ፣
አጭሩን ደግሞ ፡-
ዶሮ ሙሐሒት አሎሎ ቁመት ፣
ሰው እንዴት ይወልዳል አስመስሎ ጃርት ።

እያሉ ተጫዋቾችን እየጠሩ በተለይም የቡድኑን መሪ ከመሳደባቸውም በላይ የቡድኑን ይዘት በመጠቆም አጠቃላይ የሆነ የስድብ ግጥም ይገጥማሉ ።

ለምሳሌ ቆለኞችና ደገኞች በሚጫወቱበት ጊዜ ተሸናፊው ቡድን ደገኛ ስለሆነ ቆለኛው ክፍል ደገኛውን

«የደገኛ ጨዋ ደግ ይተዳደራል ፣
ዘመቻ ሲታዘዝ ባቄላ አሹቅ ይላል »

ብሎ ስለሰደበው ደገኛው ቡድን ደግሞ በተራው ቆለኛውን ስላሸነፈ

«ማታ ነው ድሌ ይኸው ነው አመሌ
«ማታ ነው ድሌ ይኸው ነው አመሌ»
አለና « ዝናም እንኳን አልጣለ አንጣሪያ አላወጣ
ከእንግዲህ ቆለኛ መወቂያሽ ቀን መጣ »

በማለት በግጥም ብድሩን ይመልሳል የገና ጨዋታ ግጥም በዚች ብቻ የሚወሰን አይደለም መልካም የሥራ ሹማምንት የሚሞገሱበት በትክክል ያልሠሩ ስህተታቸው የሚጠቆምበት በዚህ በገና ግጥም ነበር ።

ለማስረጃም ያህል በቀድሞ ጊዜ መልከኛ ወይም ባላባት የተባለ አጥቢያ ዳኛ ጸሐፊና ኳድሬ በየሀገሩ ይሾም ነበረና እነሱ ተባብረው በዓመት በዓል ጊዜ እጅ መንሻ ፣ ግብር ፣ በአውድማ ላይ እምሽና እርቦ ወዘተ እያሉ ሕዝቡን ያስቸግሩትና ይበዘብዙት ስለነበር በአንድ ሀገር እንዲህ ተብሎ ተገጠመ ይባላል ።

«ምኒልሢ ከቶ ምናልንህ ፣ በገበሬ የላክበት አውሬ ፣
ከአውሬም አውሬ ጣፊና ኳደሬ »

በማለት ፣ ብሶታቸውን እንደገለጡ ይነገራል ። በጤፍ ውቂያ ጊዜም እንደዚሁ ይገጠም ነበር የሚሉም አሉ ።

የሚያስደንቀው ግን በዚያን ዘመን ሥልጣን ያላቸው ሁሉ የበቀል ርምጃ ለመውሰድ የሚችሉ ሲሆኑ የተሰደቡት ባለስልጣኖች ወይም ታላላቅ ሰዎች ስድቡን እየሰሙ ከሕዝቡ ጋር ከመሳቅ በቀር በቂምና በበቀል ምንም ዓይነት ሕጋዊ ወይም ሕገ ወጥ ርምጃ የማይወስዱ መሆናቸው ነው ። «በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ » ተብሎ ይዘፈን የነበረውም ስለዚህ ነበር ይባላል ። በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቶስ የሁሉ አባት የ

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

## ስለ ክርስቶስ ከክርስትና እምነት ውጭ የተሰጡ ምስክርነቶች ።

ስለ ክርስቶስና ፣ ስለትምህርቱ ከክርስትናእምነትውጭባሉሰዎች በየዘመናት እያሌ ምስክርቶች ተሰጥተዋል ። የተሰጡት ምስክርነቶች ግን እንደ ሰዎቹ አመለካከት ይለያያሉ ። ሩቅ ባሉት ዘመናት ከተጻፉት አንዳንዶቹ በቀጥታ ስለ እርሱ የሚያወሱ ሲሆኑ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በክርስቲያኖች ላይ ሲደርስ የነበረውን መከራና ስቃይ አስመልክተው ከጻፉ ሰዎች ብዕር በተዘዋዋሪ የተገኙ ጽሑፎች ናቸው ። ከእነዚህም ጽሑፎች አንዱ ዛሬ በብሪቲሽ ቤተ መዘክር የክብር ሥፍራ ተሰጥቶታል ። ይህ ጽሑፍ የተጻፈበት ዘመን ምንም እንኳ በውል ተለይቶ ባይታወቅም በ73 እና በ80 ዓ. ም . መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፈ መሆኑን ተመራማሪዎች ገልጸዋል ። የተጻፈው በሱርስት ቋንቋ ነው ። ጸሐፊው ማራ ባር ሰራጵዮን ይባላል ። ለልጁ ለሰራጵይን የጻፈው ነው ። ጽሑፉ እንደሚከተለው ይነበባል ። «... ........ አቴናውያን ሶቅራጥስን በመግደላቸው ያገኙት ጥቅም ምንድነው? በእርሱ ላይ ከፈጸሙት በደል የተነሳ ብድራቱን በረሃብ ፣ በቸነፈር ተከፈሉት እንጂ ፣ የሳሞስ ሰዎችስ ፒታጎራስን በእሳት በማቃጠላቸው ምን ጥቅም አገኙ? ወዲያውኑ አይደለም እንዴ ምድራቸው በአሸዋ የተደፈነው ? ሕዝብ አይሁድስ ብልሕና አዋቂ የሆነ ንጉሣቸውን ክርስቶስን በመግደላቸው ምን ተጠቀሙ ? ሐገራቸው እንዳልነበር ሆና የጠፋችው ከዚያን ጊዜ በኋላ አይደል ? የእነዚህ ሦስት ታላላቅ ሰዎች ደም በከንቱ ፈስሶ የቀረ አይደለም ። ብድራቱ ወዲያውኑ በሚገባ ተከፍሏል እነሆ አቴናውያን (ግሪኮች ) በረሃብ ሲቀጡ ፣ የሰሞስ ሰዎችን ምድር ፣ የባሕር ወጀብ ያስነሳው አሸዋ ሲደፍነው ፣ አይሁድ በጠላቶቻቸው ድል ተመትተው ፣ ከሐገራቸው ፈልሰው ተሰደው በየሀገሩ ተበታትነዋል ። ....» ይላል ። ጸሐፊው ክርስቲያን አይደለም አለመሆኑም ክርስቶስን ከእነ ሶቅራጥስ ከእነ ፒታጎራስ ጋር በማነፃፀሩ ይታወቃል ። ግን ክርስቶስ ንጉሥና ብልህ ታላቅ ሰው መሆኑን አረጋግጧል ።

ሌላው ምስክርነት ደግሞ የፕሊን ጽሑፍ ነው ። ፕሊን ከ98 - 117 የሮማ ቄሣር በነበረው በትራጃን ( ትራያኖን ) የቢታንያ አገረ ገዥ ሆኖ የተሾመ ሮማዊ ነው።ቢታንያ በትንሹ እስያ ውስጥ የምትገኝ ፣ ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ላይ መከራና ስደት በመጣበትጊዜ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ተሰደው ከኖሩባቸው አውራጃዎች አንዷ ናት ። (1ኛ ጴጥ. 1 1-2 ።)

ቄሣር ትራጃን ምንም እንኳን እንደ ኔሮን ቄሣር ስሙ በጨካኝነት ባይነሳም ስለ ጣዖታት አምልኮ ፍቅር ብቻ ሳይሆን ፣ የክርስትና ሃይማኖት በዚያ ጊዜ አዲስ በመሆኑ በክርስቲያኖች ላይ ስጋትና ጥርጣሬ ስለነበረው ማናቸውም እንቅስቃሴአቸው የሚጠበቀው በዐይን ቁራኛ ነበር ። ከዚህም የተነሳ ክርስቲያኖች የሃይማኖታቸውን ሥርዐት የሚፈጽሙት በድብቅ ነበር ። ስለዚህ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ወይም እንቅስቃሴአቸውን ለመቆጣጠር የተሠራ ቋሚ ሕግ ፣ የወጣ አዋጅ ባለመኖሩ በየዕለቱ ቁጥራቸው እየጨመረ መሄዱ በቸልታ መታለፍ የሌለበት መሆኑን በመገንዘብ ብቻ ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት መመሪያ እንዲሰጠው ፕሊኒ ለትራጃን በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የሚከተለው ሰፍሯል ።

«.:...... ክርስቲያኖች ለጣዖታት መሥዋዕት አናቀርብም ፣ ላንተ ምስል አንሰግድም ከማለታቸው በቀር ፣ ሌላ ጥፋት ሌላ በደል የለባቸውም ። በየሳምንቱ እሁድ ጥዋት ገና የፀሐይ ጮራ ሳይፈነጥቅ እየተሰበሰቡ በመዘመር ክርስቶስን እንደ አምላክ ያከብሩታል ፡- ያመሰግኑታል ።

ክስርቆት ፣ ከማታለል ፣ ከቅሚያ ከዝሙትና ከመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ የራቁ ናቸው ..... » ይላል በዚያ ዘመን የነበሩት የእነዚህ ክርስቲያኖች ሕይወት« መልካሙን ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን ያመስግኑት ዘንድ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት የበራ ይሁን » ያለውን የጌታ ቃል በግብር እንዲገለጥ ያደረገ በመሆኑ ፣ ታላቅ መምህርነቱ በአሕዛብ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲደነቅ አድርጓል ። ይህም ፕሊኒ ለትራጃን በጻፈው ደብዳቤ ላይ የሰጠው ምስክርነት የክርስቶስን ታላቅ መምህርነት የሚያንፀባርቅ ፣ ክርስቲያን ካልሆነ ወገን የተሰጠ ምስክርነት በመሆኑ በየዘመኑ የተነሱ ታሪክ ጸሐፊዎች በየመጻሕፍቶቻቸው ጠቅሰውታል ።

በቁርአን ስለ ክርስቶስ ብዙ ቦታ ተጠቅሷል ። የእስልምና ሃይማኖት መሥራች የሆኑት መሐመድ ምንም እንኳ የክርስቶስን አምላክነትና መድኃኒትነት ባይቀበሉም በየዘመናቱ ከተነሱት ታላላቅ የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደ አንዱ ይቆጥሩታል ። ሕገ ኦሪት ተውራት / ለሙሴ ፣ መዝሙር (ዜቡር) ለዳዊት ፣ እንደተሰጠ ወንጌልም (ኢንጅል) ለኢሳ (ኢየሱስ) ከላይ የተሰጠ መሆኑን ያረጋግጣሉ ። ይልቁንም ክርስቶስ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ያለ ዘርአ ብእሲ በድንግልና ተጸንሶ የተወለደ መሆኑን ያምናሉ ። ( ቁርአን ምዕ . 66 ቁ . 12) ይህ እንግዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ስለ ክርስቶስ በሕቱም ድንግልና መወለድ የተሰጠ ምስክርነት መሆኑ ነው ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ካሉት የሃይማኖት መሥራች ይህን የመሰለ ምስክርነት ማግኘት ቀላል ነገር አይደለም ምንም እንኳ የክርስቶስን አምላክነት ባይቀበሉትም፣ይህ አገላለጽ ብቻ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የልዩ ልዩ ንዋየ ቅዱሳት ሥራዎችን ማዘጋጀት፣ ካህናት በተግባረ ዕድ ሙያ እንዲሰለጥኑ ማድረግና የተግባረ ዕድ ሥራዎችን ማቋቋም፣ የጓሮ አትክልትና ሰፋ ያለ እርሻዎችን መጀመር ለምእመናን የሙዳየ ምፅዋትና የአስራት አስተዋፅኦን ማስለመድ፣ የትምህርት ሂደትን ማጠናከርና የሁሉም ዝንባሌ ወደ ትምህርት እንዲያመራ መጣጣር ለልማት መነሻ ከሚሆኑት ጥቂቶቹ ናቸው ።

በዚህ ዝግጅት የምናቀርበው በአርሲ ሀገረ ስብከት ፣ በጭላሎ አውራጃ በኮፈሌ ወረዳ ርእሰ ከተማ ውስጥ በኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ካህናትና ሰበካ ጉባኤ እንዲሁም በሰበካው ምእመናን ትብብር ስለተከናወነውና ለወደፊትም ሊከናወን ስለታቀደው የልማት እንቅስቃሴ ነው ።

በኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስለተከናወነው የልማት እንቅስቃሴ የሰበካው ጉባኤ ም/ሊቀመንበር ባላምበራስ በቀለ ደንበለው በድርጅታችን ተገኝተው አንዳንድ ማብራርያወችን ሰጥተውናል ።

ሲያብራሩም የኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብሎ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ መንፈሳዊ ግልጋሎቱ እየተሟላለት ቆይቷል ።

ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በራስዋ እንድትረዳ የሰበካ ጉባኤ ደንብ “ቃለዓዋዲ ከወጣ ወዲህም ሰበካ ጉባኤ ተቋቁሞና ተጠናክሮ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት የሚፈለገውን ሁሉ በመሟላት አገልግሎቱ በተግባር እየተካሔደ ነው ።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት የጸኑ ምእመናን ሁሉ በሰበካ ጉባኤው ዓላማ አምነው ያለምንም ችግር በማኅበረ ምእመናን ተመዝግበው ዓመታዊ መዋጮአቸውን እየከፈሉ በመሆናቸው ቃለ አዋዲውን በሥራ ለመተርጐምም ሆነ ለማስተርጐም ችግር አልገጠመንም ።

ለምሳሌ ለሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት ለማሠራትና ለካህናቱ በቂ ደመወዝ ለመክፈል እንዲቻል ባደረግነው ቅስቀሳ ምእመናኑ የዓላማችን ደጋፊ በመሆን ከዓመታዊ መዋጮአቸው ሌላ ለልማት እንቅስቃሴ ገንዘብ በመክፈላቸው ካህናቱን በልማት ሥራ ለማሠማራት እያስቻለን ነው ።

ካህናቱ የሰበካ ጉባኤ አቅዋም ካልተጠናከረ በኑሮአቸው የሚረዱበት ዋስትና እንደማይኖራቸው በማመን ለሰበካ ጉባኤ መጠናከርና ለልማት እንቅስቃሴ ያላቸው ተሳትፎ እጅግ በጣም አስደሳች በመሆኑ የሥራቸው ውጤት እያረካቸው ነው ።

1- ከዚህ በፊት በዓመት 15.00 ያገኝ የነበረው ቄስ ዛሬ በወር ብር 30.00 ሲከፈለው በዓመት 360.00 ሶስት መቶ ስድሳ ያገኛል ማለት ነው ።

2- በዓመት 10.00 ይከፈለው የነበረ ዲያቆን ዛሬ በወር 24.00 የሚከፈለው ሲሆን በዓመት ብር 288.00 ያገኛል ።

3. መሪጌታ በዓመት 20.00 ሲከፈለው የነበረ ዛሬ ብር 45.00 በወር ይከፈለ



ባላምባራስ በቀለ ደንበለው

ዋል በዓመት ሲደመር ብር 540.00 ነው ማለት ነው በዚህ የሰበካ ጉባኤው አስተዳደር የሥራ ውጤት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ተደስተው ሁሉም ለልማት ወደልማት ያሉ ናቸው ። እኛም የልማቱ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ለካህናቱ ከ100.00 በላይ ደመወዝ እንደምንከፍል ተስፋ አለን ይልቁንም ነቢዩ ዳዊት “ በልቤ ደስታን ጨመርህ ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ” የሚለውን ደስታ የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች እንደሚጐናጸፉም እናምናለን የሠራ በሥራው ውጤት ይረካልና በማለት ባለላምበራስ በቀለ በዝርዝር አስረድተዋል ።

የሰበካ ጉባኤው እንቅስቃሴና ብርቱ ጥረት ካህናቱን ብቻ ሳይሆን ምእመናንን ጭምር በማስተባበር የልማቱን ሥራ በይበልጥ ለማጠናከር ነው ፣ በተለየም የሀገረ ስብከቱ ትብብር ባይለየን ካህናቱን በሙያ ማሻሻያና በስብከት አሰጣጥ ዘዴ ኮርስ አሰልጥኖ ለቤተ ክርስቲያኑና ለሚያገለግሉት ሕዝብ የተሻለ አሠራርን ለመፍጠር የማያቋርጥ እቅዳችን ሲሆን ይህ እቅድ ከሀ/ ስብከቱ ጋር ወይም ለዚህ ሥራ ቀና አመለካከት ካለው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያ ድርጅት ጋር በመነጋገር በቅርብ ጊዜ በሥራ እንዲተረጐም እናደርጋለን ብለዋል ።

ቀጥሎም ሲያብራሩ በቃለዓዋዲው ምዕራፍ 4 ዓንቀጽ 12 በሚያመለክተው መሠረት በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሊቋቋሙ ከሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች በመቋቋም ላይ ስለሚገኙ እኛን ብቻ ሳይሆን ተመልካቹንም እያስደሰተ ነው ።

ለምሳሌ 1- ትልቅ አዳራሽ ከ800 በላይ ሰዎችን የሚይዝ
2- ለሰበካ ጉባኤው ጽ ቤትና ክርስትና ማንሻ
3- ለንዋየ ቅዱሳት ማከፋፈያ የሚሆን ሱቅ እነዚህ ተሠርተው አገልግሎት

በመስጠት ላይ ናቸው ። በተለይ የንዋየ ቅዱሳት ማከፋፈያው ሱቅ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር በር ላይ በመሠራቱና የሚሸጡት ዕቃዎች በቀላል ዋጋ በመሆናቸው ተገልጋዩ እጅግ በጣም ከመደሰቱም በላይ በልማቱ አቅጣጫ ጥሩ የገቢ ምንጭ አስገኝቶልናል ብለዋል ።

ባለምባራስ በቀለ ስለ ልማቱ ጉዳይ ደጋግመው ሲናገሩ ልማት ገንዘብ የሚያስገኘው ነገር ሁሉ ነው ካህናቱ የንስ



www.ethiopianorthodox.org

ሐ ልጆቻቸውን አስተምረው ለገንዘብ አስተዋጽኦ ሙሉ ፈቃደኞች ሲያደርጉአቸው ልማት ነው ፣ በዚህ አባባል ወደ ዋናው የልማት እቅድ ለመግባት በመጀመሪያ ውኃና መብራት ያስፈልጋል ስለዚህም በቅድሚያ ኤሌክትሪክ አስገብተናል ። ይህም በመሆኑ በጧፍና በሻማ በኩል ይወጣ የነበረው ገንዘብ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር ሲነፃጸር ከከፍተኛ ወጭ ሲያድነን ችሏል ።

ከዚህም ሌላ ውሃ በቧምቧ ለማስገባት ባደረግነው ጥረት እቅዳችን ከሞላ ጐደል እየተሟላልን ስለሆነ በቅርብ ጊዜ እንደምናስገባ ተስፋ አለን ካሉ በኋላ ፣ " በእርሻህ ቡሩክ ትሆናለህ የሆድህ ፍሬ የምድርህም ፍሬ ቡሩክ ይሆናል " በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ልማት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን በማመን ካህናቱ በቤተ ክርስቲያን ክልል ቦታ ላይ በጓሮ እርሻ የየራሳቸውን የእርሻ ቦታ በማጠር ሙከራ እያደረጉ ነው ፣ ከዚህ ጠባብ ሙከራ በመነሳት ለወደፊት ወደሰፊ እርሻ ለመራመድ በሥራ የሚገለጽ እቅድ አለን በማለት ባላባራስ በቀለ ደንበለው አስረድተዋል ።

ስለቤተክርስቲያኑ እድሳትና ድምፅ ማጉያ ማስገባት ጉዳይ ሲያብራሩ ቤተ ክርስቲያኑ ከተሠራና እድሳትም ካገኘ ዘመኑ በጣም ራቅ ያለ ስለ ነበር ፈራርሶ የነበረውን ጣራና ግድግዳ ፣ መዝጊያና መስኮት ፣ ሌላውንም ክፍል በመጠገን አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው ፣ ከዚህም ሌላ የጣራው ዙሪያ ክፈፍ መርገፍ እንዲገባለት ተደርጎ ሥራው በመከናወን ላይ ነው ።

የድምፅ ማጉያ ማስገባት የግድ አስፈላጊ በመሆኑም ምእመናንን እና ድርጅቶችን በማስተባበር ከብር 1.00 - 500 በማዋጣት ብር 4.320.00 ለፊልፕስ ኩባንያ ተከፍሎ ድምፅ ማጉያ በመግባት ላይ በመሆኑ የተባበሩና ያስተባበሩትንም በዚህ አጋጣሚ ላመሰግን እወዳለሁ ብለዋል ።

አዎ ቤተ ክርስቲያን ካለባት ጊዜአዊ ችግር ትላቀቃለች የካህናቱም ደካማ ኑሮ ይሻሻል ተብሎ ተስፋ የተጣለው የሰበካ ጉባኤ አቅዋም ሲጠናከርና ካህናት የልማት ሥራን ሲለምዱ ነው። ከዚህም ሌላ በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ 52 እና 53 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሰበካው ካህናትና ምእመናን በገንዘብ አስተዋጽኦ ፣ በአስተዳደር ፣ በልማትና በማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ሲስማሩና በጠቅላላው በሀብት ፣ በዕውቀትና በጉልበት ለልማት ሥራ ተሰትፎ ለማድረግ ሲችሉ ነው ።

ስለዚህም ልማት ሲባል እህልን የሚያስገኝ እርሻ ብቻ ማረስ አለመሆኑ ታውቆ ከእርሻ ልማት ጋር የእደ ጥበባት ሥራዎች ታክለው ቤተ ክርስቲያን በውስጥም ሆነ በውጭ የምትገለገልባቸው ንዋየ ቅድሳት በካህናቱ እየተዘጋጁ ለአገልግሎት እንዲቀርቡ ጥረት ማድረግ ያሻል ።

ይህ በሥራ ሲተረጐም የቤተ ክርስቲያን አመራር ይጠናከራል ፣ የካህናቱ ደካማ ኑሮ ያድጋል በጠቅላላው ከሌሎች ታመጣና ትገበይ የነበረች ቤተ ክርስቲያን፣ በካህናቱና ምእመናኑ ትብብር ባስገኘችው የልማት ውጤት ለሌሎች ልትረዳ እንደምትችል አንጠራጠርም ፣ ሰው ካልዘራ አይሰበስብም ፣ ከዘራ ግን የዘራውን በመሰብሰብ በውጤቱ ሊደሰት ይችላልና ።

በለጠ አበበ

## ይህን ያውቁ ኖሯል ?

ከገጽ ፳፱ የዞረ

የክርስቶስን ከሃሊኩልነት( ሁሉን ቻይነት ) አጉልቶ የሚያሳይ ምስክርነት ነው ለማለት ይቻላል ።

በዘመናችንም ስለ ክርስቶስ ታላቅነት ከክርስትና እምነት ውጭ ባሉ ወገኖች የተሰጡ የሚያስደንቁ ምስክርነቶች አሉ ። ሁለቱ ብቻ ባጭሩ ቀጥሎ ቀርበዋል ። መስካሪዎቹ የሕንዱይዝም እምነት ተከታዮች ናቸው ። ይህም ብቻ አይደለም ። ሁለቱም በምስራቁ ዓለም ፈልስፍናና በዘመናዊ ትምሕርት የበሰሉ ናቸው ። ቪቪካናንዳና ማህአተማ ጋንዲ ይባላሉ ። በመሠረቱ ሁለቱም ለሃይማኖቶች ሁሉ ከፍ ያለ አክብሮት አላቸው። ለክርስትና እምነት ያላቸው አመለካከት ግን የተለየ ነው ። ይልቃል ።

ቪቪካናንዳ የምዕራቡን ዓለም ዞሮ በሚጐበኝበት ጊዜ ሮማ ከተማ ሳለ አንድ ደቀ መዝሙር «ምስለ ፍቁር ወልዳ» የእመቤታችንን ስዕል አቅርቦ « እባክ ባርክህ ስጠኝ » ብሎ ቢጠይቀው የሕፃኑን የክርስቶስን እግር ትልቅ አክብሮት በሚታይበት ትሕትና በእጁ ዳስሶ ፣ « እግሮቹን በእንባዬ ባጥብ በወደድኩ ነበር » ብሎ ሳይባርክ ስዕሉን መለሰለት (ሥልጣኔ ማለት ምንድነች ? ከከበደ ሚካኤል ገጽ 50 ።

ማሕአትማ ጋንዲ ስለ ክርስቶስና ስለ ትምህርቱ የነበረው ፍቅርና አክብሮት ከማንም የተለየ ነበር ።ልቡ በክርስቶስ ትምህርትና ፍቅር እጅግ የቆሰለ ሰው ነበር ። ግን ክርስቲያን አልነበረም። የክርስትናን እምነት እንዳይቀበል እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች አንዱ ፣ ክርስቲያን ነን የሚሉት ቅኝ ገዥዎች ለጥቅም ሲሉ ይፈጸሙ የነበሩትን ግፍና በደል በመመልከት ጥላቻ አድሮበት ነው ያሉ አሉ ። ለመሆኑ ? እኒህ ምዕራባውያን «የተራራ ላይ ስብከት » ( እንደ እኛም ቤተ ክርስቲያን አባባል አንቀጸ ብፁዓን የሚባለውን በማቴዎስ ወንጌል ምዕ .5 ከቁጥር 1 እስከ መጨረሻው የሚገኘውን ) የት አድርገውት ነው ለጥቅም ሲሉ ይህን ግፍና በደል በሰው ሀገር የሚፈጽሙት እያለ ዕድሜውን ፈጅቷል ። ዶክተር ኢ . እስታንሉይ ጆንስ የተባሉ አሜሪካዊ የወንጌል መልእክተኛ ጋንዲን «ክርስቶስን በግብር ከመሰሉት እርሱ ግን ክርስቲያን ያይደለ ፣ የይስሙላ ክርስቲያንነት ትክክለኛ ትርጉሙን እንዲ

ወደ ገጽ ፲፰ የዞረ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org